# አዲስ ዘመን

እናድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 229 ሚያዝያ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

# የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራ አበረታች መሆኑን ምክር ቤቱ ገለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እያከናወነ ያለው የቅድመ ዝግጅት ሥራ ታሪካዊውን አገራዊ ጉዞ ሊያሳካ የሚችል አበረታች ሥራ እንደሆነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን የተግባርና እቅድ ዘገባ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አመራሮችና የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች አቅርቧል፡፡ በመድረኩም የሕዝብ እንደራሴዎች ኮሚሽኑ ባለፉት ሁለት ወራት ያካሄዳቸው የቅድመ ዝግጅት ተግባራት አበረታች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም ለአገሪቱ ዜጎች ተስፋ ሰጪና የታሰበውን አገራዊ ታሪካዊ ጉዞ ለማሳካት የሚያስችል ጅማሮ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ፣ የዝግጅት ምዕራፍ፣ የምክክር ሂደት ምዕራፍና የምክክር ውጤቶች መተግበሪያ ምዕራፍ በሚል ሂደቶችን

የአገራዊ ምክክር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

## ‹‹የረመዳን ወር ቀሪ ቀናትን በመረዳዳትና በመከባበር ማሳለፍ ይገባል››

-ሼህ መሐመድ ሲራጅ
የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ዑለማ ምክር ቤት አባልና የሰላምና እርቅ ዘርፍ ኃላፊ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ ፡- የእስልምና እምነት ተከታዮች የረመዳን ወር ቀሪ ቀናትን የተጎዱ ወገኖችን በመርዳትና በመተሳሰብ ማሳለፍ እንደሚገባቸው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ዑለማ ምክር ቤት አባልና የሰላምና እርቅ ዘርፍ ኃላፊ ሼህ መሐመድ ሲራጅ ገለጹ፡፡

ሼህ መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የረመዳን ወር ቀሪ ጊዜያትን የተቸገሩትን በመርዳት፣ በመከባበርና በመተሳሰብ ማሳለፍ ይጠበቃል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በመርዳትና በመደገፍ ማሳለፍ ያስፈልጋል፡፡

‹‹የረመዳን ወር ቀሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

# የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአንጋፋ ደራስያኑ ስም ያሰባሰባቸውን 5 ሺህ መጽሐፍት ለአብርኆት ቤተመጻሕፍት አስረከበ

## - በሃገር አቀፍ ደረጃ ለአብርኆት ቤተመጻሕፍት የመጻሕፍት ማሰባሰብ ዘመቻ ሊጀመር ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአንጋፋ ደራስያኑ ስም ያሰባሰባቸውን ከአምስት ሺህ በላይ መጽሐፍት ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት አስረከበ። በሃገር አቀፍ ደረጃ ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት የሚውል የአንድ ሚሊዮን መጽሐፍት ማሰባሰብ ዘመቻ ሊጀመር

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## ለኢድ በዓል ወደአገራቸው የሚገቡ ዲያስፖራዎች መጽሐፍትን ይዘው እንዲመጡ ጥሪ ቀረበ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ከኢድ እስከ ኢድ አገራዊ ጥሪን ተከትለው ወደአገራቸው የሚገቡ ዲያስፖራዎች የተለያዩ መጽሐፍትን ይዘው እንዲመጡ የአዲስ አበባ የባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጥሪ አቀረበ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተቋሙ በተለያዩ ጊዜ ባገለገሉ አንጋፋ ደራስያን ስም ያሰባሰባቸውን አምስት ሺህ መጽሐፍት ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት ባስረከበበት ወቅት የተገኙት ዶክተር ሂሩት ካሳው ለኢድ በዓል ወደአገራቸው የሚገቡ ዲያስፖራዎች መጽሐፍትን ይዘው እንዲመጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በወቅቱ ዶክተር ሂሩት፤ ከኢድ እስከ ኢድ የተሰኘውን አገራዊ ጥሪ ተከትሎ በርካቶች ለአገራቸው

ለኢድ በዓል ወደአገራቸው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የውጭ ምንዛሪ ድርሻን በተመለከተ የወጣው መመሪያ በወጪ ንግድ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል

-ባለሃብቶች

## • አምራች ተቋማቱ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ትክክለኛ መረጃ ሊያቀርቡ ይገባል

-የግብርና ሚኒስቴር

በግርማቸው ጋሻው



አዲስ አበባ፡- ባለሃብቶች ወደ ሃገር ውስጥ በሚያስገቡት የውጭ ምንዛሪ ገቢ ላይ የተደረገው አዲሱ የክፍፍል ቀመር ማሻሻያ ወደ ውጭ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ጥራትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል በአበባና ፍራፍሬ አምራችና ላኪነት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ተናገሩ። የግብርና ሚኒስቴር በበኩሉ አምራች ተቋማቱ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀማቸውን የሚያመለክት ትክክለኛ መረጃ ለመንግሥት ቢያቀርቡ ችግሩን በጥናት መመለስ ይቻላል ብሏል።

ባስ ተርሎው የአበባ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የሚታወቀው አቢሲኒያ ፍላወርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የኢትዮጵያ ቢሮ አስተባባሪ ናቸው። እሳቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የውጭ ምንዛሪ ድርሻን በተመለከተ የወጣው መመሪያ በወጭ ንግድ የተሰማራ ማንኛውም ነጋዴ ካገኘው 20 በመቶ የሚሆነውን ዶላር ለራሱ እንዲጠቀም የሚፈቅድ ሲሆን ቀሪውን 80 በመቶ የሚሆነው በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ለባለሃብቱ እንዲሰጥ ያስገድዳል።

በዚህ ሕግ ምክንያት ድርጅቱ ጥራት ያላቸውን የአበባ ምርቶችን ለማምረት ከውጭ በሚያስገባቸው የማዳበሪያ፤ ኬሚካልና ሌሎች ግብአቶችን በበቂ መጠን ለማስገባት እንደተቸገረ አቶ ባስ ያስረዳሉ። ይህ በዚህ ከቀጠለ ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖረው ተወዳዳሪነት ቀንሶ ወደ ሃገሪቱ ሊያስገባ የሚችለው የውጭ ምንዛሪ በዚያው ልክ ሊቀንስ እንደሚችል ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

ቀደም ሲል የነበረው አዋጅ 30 በመቶ የሚሆነውን ዶላር ለባለሃብቱ የሚሰጥና የተሻለ እንደነበር ያስታወሱት ባለሃብቱ፤ አዲሱ መመሪያ እንዲስተካከል በአበባና ፍራፍሬ አምራቾች በኩል ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ እንደሆነም ተናግረዋል። አዲሱ የዶላር ክፍፍል ቀመር መመሪያ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ተግዳሮት እየፈጠረ ስለመሆኑም አንስተዋል።

የአቮካዶ ምርት ላይ እሴት በመጨመር ወደ ውጭ የመላክ ሥራ ላይ የተሠማራው ሰንሻዶ ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ጁስት ሄጅ የአቶ ባስን ሃሳብ ይጋራሉ። ይህ አይነቱ መመሪያ በተለይ ለአምራችና ላኪ ባለሃብቶች ተግዳሮት እንደሆነ መንግሥትም የሚገነዘበው ይመስለኛል ያሉት አቶ ጁስት፤ ይህ ጊዜያዊ እርምጃ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ከባንኮችና ከቢዝነሱ የሚደርስባቸው ጫና ይህንን ሊቀለብስ ይችላል ይላሉ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ያሉ አብዛኛዎቹ ነጋዴዎች ቡና፣ ሰሊጥ እና ሌሎች ሸቀጦች ወደ ውጭ በመላክና ወደ ሃገር ውስጥ ለሚያስገቡት እቃ ዶላር ለማግኘት የሚጥሩ ናቸው ብለዋል።

ጉዳዩን በተመለከተ ምላሽ የሰጡት በግብርና ሚኒስቴር በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ዘርፍ የኤክስፖርት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክተር መኮንን ሰሎሞን መንግሥት የወሰደው ይህ እርምጃ ጊዜያዊ ነው። ችግሩ በተግባር በሚታይበት ጊዜ እየተነሳ ያለውን ቅሬታ ወይም አቤቱታ ትክክለኛነት በጥናት ማጣራትና ምላሽ መስጠት እንደሚገባም ገልጸዋል። የአበባ አምራች ተቋማቱ ራሳቸው የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀማቸውን በተመለከተ መረጃ መስጠት አለባቸው። ከአትክልትና ፍራፍሬ አምራቾችና ላኪዎች ማኅበርም በቂ መረጃ እየቀረበልን አይደለም። ከዚህ አንጻር አንዳንድ ቅሬታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ትክክለኛ መረጃ ቢገኝ አማራጭ መፍትሔ ማፈላለግ ይቻላል ሲሉ አቶ መኮንን አስረድተዋል።

አዲሱ አዋጅ በብሔራዊ ባንክ ወጥቶ ከባለፈው ጥር 28 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወሳል።



ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ

# አካል ጉዳተኞች በተደራጀ መንገድ የሚያካሂዱት ትግል አድልዎና መገለልን እያስወገደ ነው

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- አካል ጉዳተኞች በተደራጀ መንገድ የሚያካሂዱት ትግል አድልዎ እና መገለልን እያስወገደ መምጣቱን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

በ25ኛው የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን የምሥረታ ክብረ በዓል የተገኙት የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ፤ አካል ጉዳተኞች የሚያካሂዱት ትግል ሲደርስባቸው የነበረውን አስከፊ የአድሎና መገለልን እያስወገደ መምጣቱን አመልክተዋል።

በአካል ጉዳተኞች ላይ ሲደርሱ የነበሩት የመገለልና አድልዎ ተግባራት ስፍራቸውን ለእኩል እድል እየለቀቁ ይገኛሉ።ለዚህ ውጤት መገኘት የአካል ጉዳተኞች በተደራጀ መንገድ መንቀሳቀሳቸው በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው።ተግባሩም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ማንኛውም ሰው ከውልደት እስከ እለተ ሞት ድረስ በማይክሮ ሰከንዶች ውስጥ የአካል ጉዳት ሊከሰት ይችላል።ክስተቱ በሰከንዶች ሊፈጠር የሚችል በመሆኑ ጉዳዩን የጋራ አድርጎ ከልብ መሥራት ያስፈልጋል፣ ጉዳዩን ለአካል ጉዳተኞች ብቻ ሊተውና ሊገፋ እንደማይገባውም ዶክተር ኤርጎጌ ተናግረዋል።

ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የሚሰጥ አካታችነት ያለው አሠራርም በየተቋማቱ ጎልቶ ሊወጣ እንደሚገባ በማመልከትም፤ የአካል ጉዳተኞች መብት፣ ጥቅምና ተሳትፎ እንዲከበር የሚደረገው ጥረትም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባውም ነው የጠቆሙት።

አካል ጉዳተኞች ለዘመናት ከተሳትፎና ተጠቃሚነት ተገፍተው እንደኖሩ ያስታወሱት ሚኒስትሯ፤ መብትና ጥቅሞቻቸውን ለማክበርም መንግሥታት፣ የአካል ጉዳተኛ ማኅበራትና አካል ጉዳተኞች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ማኅበረሰቡ እየተሻሻሉ የመጡ ሕጎችን እየተገበሩ እንደሚገኙ አመልክተዋል።

በጎጂ ልማድ፣ በተዛባ አመለካከት፣ በአግላይ ሕግጋትና በመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳም አካል ጉዳተኞች ተጋፍጠውት የነበረው ችግር ውስብስብና ለዘመናት ትውልድ የተቀባበለው ዘርፈ ብዙ መከራ እየገፉ አሳልፈዋል ብለዋል።

ይህ አስከፊ ገጽታ እንዲቀየርም በመንግሥታት፣ በአካል ጉዳተኛ ማኅበራትና በአካል ጉዳተኞች፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና በአጠቃላይም በማኅበረሰቡ በኩል እየተደረገ ባለው ጥረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጨባጭ ለውጥ መታየት መጀመሩን ተናገረዋል።

25ኛው የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን ምስረታ "ጉዟችን ይቀጥላል" በሚል መሪ ሐሳብ ተከብሯል። በዓለም አቀፍ ከአንድ ቢሊዮን በላይ አካል ጉዳተኞች፣ በኢትዮጵያ 20 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ከተለያየ ዓይነት የአካል ጉዳት ጋር እንደሚኖሩ መረጃዎች ያመለክታሉ።

# ፊቼ ጨምበላላ ሰላም፣ አንድነትና ፍቅርን ለማጠናከር ያለውን እሴት ጠብቆ በድምቀት እንደሚከበር ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

**አዲስ አበባ፡-** ፊቼ ጨምበላላ የሃገርን ሰላም፣ አንድነትና የእርስ በርስ ፍቅርን ለማጠናከር ያለውን እሴት ጠብቆ በልዩ ድምቀት እንደሚከበር የሲዳማ ክልል ምክር ቤት ዋና አፈ- ጉባኤ ፋንታዬ ከበደ አስታወቁ።

የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ የፊቼ ጨምበላላ በዓል አስመልክተው ዋና አፈ- ጉባኤዋ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በዚሁ መልዕክታቸው፤ የሲዳማ የዘመን መለወጫ በፈጣሪ እርዳታ ዘመን የሚሻገሩ ዜጎች በጋራ ፈጣሪያ ቸውን የሚያመሰግኑበት የፍቅርና የአንድነት በዓል ነው ብለዋል፡፡

በዓሉ በሚከበርበት ወቅት ከሰውን እስከ እንስሳት እንዲሁም ለእጽዋትና አራዊቶች ጨምሮ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚደረግበት ሥነ-ሥርዓት መሆኑን አንስተዋል፡፡

አባቶች በ"ቄጣላ" ሴቶችና ልጃገረዶች "ሆሬ" ወጣቶችና ልጆች በ"ፋሮ በነጻነት የሚቦርቁበትና በጋራ የሚጫወቱበት ባህላዊ ክንዋኔ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም የወደፊት አንድነታቸውን እያጠበቁና እያጠናከሩ እንዲሄዱ የሚያደርግ የበዓል አከባበር ሥርዓት ነው፡፡

ዋና አፈ-ጉባኤዋ እንዳብራሩት፤ በዓሉ የብሔሩ ተወላጆችና ሌሎችም በአደባባይ አብሮ በመብላት



የሲዳማ ክልል ምክር ቤት ዋና አፈ- ጉባኤ ፋንታዬ ከበደ

በመጨፈር እርስ በርስ እየተሞጋገሰሱና ፈጣሪን እያመሰገኑ የሚያከብሩበት ነው።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በኮሮና ምክንያት በአደባባይ ሳይከበር ማለፉን አስታውሰዋል፡፡

አሁን ላይ ችግሩ በመቃለሉ በአደባባይ በተለያየ ትዕይንት ለማክበር ዝግጅት መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

ፊቼ ጨምበላላ የሃገርን ሰላምና አንድነት እንዲሁም በዜጎች መካከል እርስ በርስ ፍቅርን ለማጠናከር ያለው እሴት በጠበቀ መልኩ በልዩ ድምቀት እንደሚከበር አስታውቀዋል፡፡

የተጣሉት ሁሉ የሚታረቁበት፣ ከቂምና በቀል የሚነጹበት የነገይቱን ተስፋና ሰላም የሚያጸኑበት የጋራ በዓል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዓሉ በሰላም እንዲከበር ለማስቻል ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰው፤ እያንዳንዱ ነዋሪ አካባቢውን እየጠበቀ ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን የድርሻውን እንዲወጣ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በተለይም በዜጎች መካከል ፍቅርና አንድነት እንዲሁም የሥራ መነሳሳትና ብሔራዊ መግባባት ከፍ ብሎ የሚያታይበት በዓል እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

በሚያዚያ 20 እና በ21 በተለያዩ ዝግጅቶች በሚከበረው የፊቼ ጫምባላላ በዓል ላይ የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተወካዮችና አፈ- ጉባኤዎች ጨምሮ የተለያዩ እንግዶች እንደሚታደሙ ይጠበቃል፡፡

የፊቼ ጨምባላላ በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርስነት ከተመዘገበ ስድስት ዓመታትን ማስቆጠሩ ተመል ክቷል።

# በሱማሌ ክልል በተከሰተው ድርቅ፡-

- ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሕዝብ ለምግብ እጥረት ተዳርጓል
- አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የቁም እንስሳት ሞተዋል
- ሁለት ሺ 305 ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- በሱማሌ ክልል በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሕዝብ ለምግብ እጥረት መዳረጉን እና ሁለት ሺ 395 ትምህርት ቤቶች በከፊልና ሙሉ በሙሉ መዘጋታቸውን የክልሉ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ቢሮ ገለጸ።

የክልሉ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሳዲቅ አብዱልቃድር ከሊፍ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተከሰተው ድርቅ በርካታ የክልሉ አካባቢዎችን ጎድቷል።በባለፈው 2013 ዓመት የመኸርና የበልግ ወቅቶች በቂ ዝናብ ባለመገኘቱ ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለመጠጥ ውሃ እጥረት፣ ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚሆው ሕዝብ ደግሞ ለምግብ እጥረት ተዳርጓል።



ፎቶ በጸሐይ ገጉቤ

አቶ ሳዲቅ አበዱቃድር ከሊፍ

እንደ አቶ ሳዲቅ ገለጻ፤ ለክልሉ ሕዝብ መሠረታዊ ሀብት የሆኑ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆኑ የቁም እንስሳት ሞተዋል።በዚህም ምክንያት ከአምስት ዓመት በታች ጡት የሚያጠቡ እናቶች ለአልሚ ምግብ እጥረት ተዳርገዋል።

ድርቁ ባስከተለው ጉዳት ሁለት ሺ 305 ትምህርት ቤቶች በከፊልና ሙሉ በሙሉ መዘጋታቸውን የገለጹት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ውጭ ሆነዋልም ብለዋል።

ለድርቁ ምላሽ ለመስጠት በተከናወኑ ተግባራት እስካሁን በአስር ዞኖች በ84 ወረዳዎች ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ለሚሆን ሕዝብ በቦቴ አማካኝነት የመጠጥ ውሃ ማድረስ ተችሏል።

አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ለሚሆነው ሕዝብ ደግሞ በመንግሥት በጀትና በተለያዩ ክልሎችና ረጂ ድርጅቶች አማካኝነት ምግብ እንዲደርስ መደረጉን አቶ ሳዲቅ ተናግረዋል።

ድርቁን ለመቋቋም ክልሉ የመስኖ ልማት ሥራ እቅድ ነድፎ እየሠራ መሆኑን የገለጹት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ድርቁ ካደረሰው ጉዳት አንጻር እየተደረገ ያለው ድጋፍ አነስተኛ ነው።

በክልሉ በአሁኑ ጊዜ ድጋፍ እየተደረገ ያለው ለሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሕዝብ ሲሆን ድጋፍ ከሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች አንጻር በቂ አይደለም።ሕዝቡን ለመደገፍ ከክልሉ አቅም በላይ በመሆኑ የፌዴራል መንግሥትን ጨምሮ የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ረጂ ድርጅቶች፣ ማኅበራትና ሌሎች በጎ አድራጊዎች የክልሉ ሕዝብ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

# የፊቼ ጨምበላላ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ በቂ ዝግጅት መደረጉን የከተማዋ ፖሊስ መምሪያ ገለጸ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- የፊቼ ጨምበላላ የሲዳማ ዘመን መለወጫ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ በቂ ዝግጅት ማድረጉን የሐዋሳ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ገለጸ።

የሐዋሳ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ ኮማንደር ደረሰ ቡሳሮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ ሚያዚያ 20 እና 21 በታላቅ ድምቀት የሚከበረው የፊቼ ጨምበላላ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ በቂ ዝግጅት ተደርጓል።

በዓሉ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር የከተማው ፖሊስ ከክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን እና ከክልሉ ሰላም እና ጸጥታ ቢሮ ጋር የጋራ ዕቅድ በማውጣት በጥምረት እየተሠራ ነው።

ችግሮችን አስቀድሞ በመለየት ዕቅድ በማውጣት በዝርዝር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች እንዳሉም ኮማንደር ደረሰ ተናግረዋል።

የሲዳማ ሕዝብ በባህሉ መሠረት "ዳኤ ቡሹ ብሎ" እንግዳ የሚቀበል ሕዝብ ነው። አስቀድሞ ሥራዎችን በመሥራትም በከተማዋ ውስጥ የንጥቂያ እና መሰል ወንጀሎችን የሚፈጽሙ አካላትን በመከታተል በሶስት ቀናት ውስጥ 66 ተጠርጣሪዎችን መያዝ እንደተቻለም ተናግረዋል።

አሁን የከተማው እንቅስቃሴ ፍጹም ሰላማዊ ነው። በዓሉን ለማክበር ከተለያዩ አካባቢዎች በርካታ እንግዶች ወደ ከተማዋ እየገቡ ይገኛሉ። በከተማዋ የበዓል ድባብ የሚታይበት ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንደሚስተዋልም ነው የጠቆሙት።

በትራፊክ እንቅስቃሴውም በኩል ጠንካራ ሥራ ተሰርቷል፣ በዓሉን ምክንያት በማድረግ የታሪፍ ጭማሪ እንዳይኖር በማኅበራት በኩል ውይይት መደረጉንም ገልጸዋል።

የፋሲካ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ማኅበረሰቡ ከጸጥታ አካላት ጋር በመተባበር ትልቅ ሚና እንደተጫወተ አስታውሰው፤ የከተማው ሕዝብ ለሰላም ዘብ የቆመና ቁርጠኝነት እንዳለውም ተናግረዋል።

ይህ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው ያሉት ኮማንደር ደረሰ፤ በቀጣይም ለሚከበሩት የፊቼ ጫምበላላ የሲዳማ ዘመን መለወጫ እና የኢድ አልፈጥር በዓላት በሰላም እንዲጠናቀቁ የሀዋሳ ከተማ ሕዝብ እንደተለመደው ከጸጥታ አካላት ጎን እንዲሰለፉ ጥሪ አቅርበዋል።

ሆቴል ቤቶችም የማረፊያ ክፍሎችን በሚያከራዩበት ጊዜ የሚያርፈውን ሰው ማንነት የሚገልጽ መታወቂያ እየጠየቁ ማከራየት እንዳለባቸው አሳስበዋል። ማኅበረሰቡ የተለየ ነገር ካጋጠመው ለከተማ ፖሊስ መምሪያ ጥቆማ መስጠት እንዳለበት ተናግረዋል።

የፊቼ ጫምበላላ በዓል የተጣላ የሚታረቅበት የሰላም በዓል እንደመሆኑ በዓሉ የፍቅር እና የሰላም እንዲሆንም መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

# ኅብረተሰቡ ከሐሰተኛ የዲጂታል ወያኔ የማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች እንዲጠነቀቅ ተጠየቀ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል ወያኔ ሕዝብን ከሕዝብ የማጋጨትና ሃገርን የማተራመስ ተግባሩን የቀጠለ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ኮርኳሪ መልዕክቶችን ተጠቅመው የጥፋት ተልዕኮ ይዘው ከሚመጡ ሐሰተኛ የማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች ሊጠነቀቅ እንደሚገባ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አሳሰበ።

ዲጂታል ወያኔ ከአካላዊ ጦርነቱ አስቀድሞ ኢትዮጵያውያንን ለማባላት፣ ለማጋጨትና እኩይ ተግባሩን ለማስፈፀም የተለያዩ ትርክቶችን እየፈጠረ እኩይ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየና አሁንም በዚህ ተግባሩ እንደገፋበት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ይግዛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ሹመቴ ገለፃ፤ ባለፉት 30 ዓመታት የተሠሩ የፖለቲካ ትርክቶችና የተሠሩ ሥራዎች ለማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች ትልቅ ግብዓት ወደ መሆን አዝማሚያ ሄደዋል።ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም አሸባሪው ሕወሓትን ጨምሮ በሃገር ውስጥና ከሃገር ወጪ ያሉ የኢትዮጵያን መልካም ነገር የማይፈልጉ አካላት በዲጂታል መንገድም ሆነ በአካላዊ ጦርነት ኢትዮጵያን ለማጥቃት ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።



ሃገሪቱ ካለችበት ቀጠናዊ ሁኔታ፣ ካለፈችበት ታሪክ እና በሃገሪቱ ካሉ የፖለቲካ ትርክቶች ጋር ተያይዞ ዲጂታል ሚዲያው ብዙ ነገሮች ሊሠሩበት የሚችል የመረጃ ጦር ሜዳ የመሆን አዝማሚያዎች ባለፉት ጊዜያት ሲካሄዱ አስተውለናል ብለዋል ዋና ዳይሬክተሩ።

ዲጂታል ወያኔ የዲጂታል ጦርነቱን በተለያየ መንገድ እየተገበረ ነው። ለአብነትም ኦሮሞ ሳይሆኑ የኦሮሞ ሥም ገፆችን በመክፈት፤ አማራ ሳይሆኑ የአማራ ሥም የያዘ ገፅ በመክፈት የብሔር ጉዳዮችን አንስቶ በመሳደብና ተቆርቋሪ በመምሰል በሐሰተኛ ገፅ ተጠቅመው ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ማዛባት ጦርነት እያካሄዱ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም በአርቲስቶች፣ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ታዋቂ ሰዎች ሥም በርካታ ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ተከፍተው ሲሠሩ በክትትል ተደርሶባቸው በሕግ የተጠየቁና ውሳኔ የተላለፈባቸው አሉ። ቁጥራቸው በርከት ያለ የሐሰተኛ መረጃ አሰራጮችና የሐሰተኛ ገፅ ተጠቃሚዎች በክስ ሂደት ላይ እንዳሉ ተነግሯል።

በተለያዩ የመ ረጃ ምንጮች ላይ ከ800 ሺህ በላይ ሐሰተኛ ማኅበራዊ የትሥሥር ገፆች ተከፍተው ሃገርን ለማተራመስ እየሠሩ ስለመሆኑ መረጃ አጣቅሰን የጠየቅናቸው ኃላፊው ቁጥሩ ከዚህ ሊያሻቅብ እንደሚችል ገልጸዋል። ዋናው ነገር ግን ከገበያ የተገኘ ሁሉ እንደማይገዛ እንዲሁ መረጃዎች ሁሉ አይገበዩም፤ ምንጫቸው መጣራት ይኖርበታል። ይህ ሲደረግ የሐሰተኛ መረጃዎች ሥርጭት እና የሚያደርሱት ጉዳት እንዲቀንስ ይሆናል ተብሏል።

ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ብቻ ሳይሆኑ ትክክለኛ አካውንቶች ሆነው ጭምር ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎችን የሚያሠራጩ እንዳሉ የገለጹት ዶክተር ሹመቴ፤ ማኅበራዊ የትሥሥር ገፆችን ለመልካም የሚጠቀመው እንዳለ ሆኖ እኩይ ዓላማ ያላቸው ሐሰተኛ መረጃዎችን በማሠራጨት የተጠመዱ በመኖራቸው ማኅበረሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ መክረዋል።

የማኅበራዊ ዲጂታል ሚዲያዎችን በአግባቡ የመጠቀም ግንዛቤ በማኅበረሰቡ ዘንድ እምብዛም መሆኑ ለሚነሳው ሐሰተኛ መረጃ ጥሩ አጋጣሚ እንደፈጠረለት የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ሥራው ጎን ለጎን ሐሰተኛ መረጃ የሚያሠራጩ የማኅበራዊ ትሥሥር ገፆችን ማዘጋት እና በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነም ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የራሱ የሆነ መሥፈርት አውጥቶ ሰፊ ክትትል እያደረገ እንደሆነና በሕግ የማስጠየቅ ተግባሩንም ሆነ ለዲጂታል ሚዲያ ባለቤቶች ሪፖርት በማድረግ ማዘጋቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰዋል።ሆኖም ዘላቂ መፍትሔ የሚሆነው ስለሐሰተኛ መረጃዎችና ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ማኅበረሰቡ አውቆና በቂ ግንዛቤ ኖሮት እንዲጠቀም ማድረግ ነው መሆኑን ተናግረዋል።

ሐሰተኛ የማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች ዋና ዓላማ ለግለሰብ የግል ፍላጎት፣ ፖለቲካዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ አለያም ማኅበራዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ፍላጎትን ማስፈፀም ነው፤ ስለዚህም በጥፋታቸው ልክ ተጠያቂ መደረግ ይገባቸዋል ያሉት ዶክተር ሹመቴ፤ ለአብነት ፌስ ቡክን አንድ ነጥብ 3 ቢሊየን ፌክ አካውንቶችን በ2021 የፈረንጆች ዓመት መጨረሻ ላይ ማጥፋቱ እና በ2022ም ይህ የሚቀጥል ይሆናል ተብሎ ስለሚጠበቅ ኢትዮጵያ በዘርፉ የምታደርገውን ትግል እንደሚያጠናክርላት ተስፋ እንደተጣለበት ጠቅሰዋል።

# የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከፋፍሎ እየተገበረ እንዳለ ተገልጿል።በዚህም አገር በቀል እውቀቶችን ሰብስቦ ከመሰነድ ጀምሮ፣ ከተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ጋር መምከሩንና አስፈላጊ ግብዓቶችን ማግኘቱን የኮሚሽኑ ዋና ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ ያቀረቡ ሲሆን፤ እስካሁን የተከናወኑ ተግባራት አበረታችና ለቀጣይ ሥራ አጋዥ መሆናቸውን በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችና አመራሮች ተነግሯል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ እንደተናገሩት፤ አገራዊ ምክክሩ ለሁሉም የምትሆን ኢትዮጵያን የመገንባት ትልቅ ፕሮጀክት ነው፤ ይህንን ለማሳካት የኮሚሽኑ ሚና የጎላ ነው።በዚህም ኮሚሽኑ ባለፉት ሁለት ወራት ዝግጅቶቹን በምዕራፍ ከፋፍሎ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑ የታለመለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል በጎ ጅምር ነው፡፡

የቅድመ ዝግጅት የክንውን ሥራው እንደ ስኬት የሚታይ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በቀጣይ ሥራውን ለሚመለከተው አካል መረጃን ተደራሽ ማድረግ እንዳለበት፤ ሥራውን በባለሙያዎች ታግዞ ማከናወን እንደሚገባውም ጠቅሰዋል።ኮሚሽኑ ለምክክር ስኬቱ የሚያከናውናቸው ተግባራትን በፍኖተ ካርታ ማስደገፍ እንዳለበትም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባዔ ወይዘሮ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፤ ኮሚሽኑ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ተቋቁሞ እስከ መጨረሻው ቁርጠኛ ሆኖ ለመሥራት እየሄደበት ያለው ርቀት ሊደነቅ እንደሚገባው ተናግረዋል።ይህ ለሌሎች አካላትም ትምህርት ሰጪ ነው ብለዋል።ኮሚሽኑ ምን እየሠራ እንደሆነ ለሕዝብ ማሳወቅ የሚችልበትን ተግባቦት ማጠናከር፤ የሕዝቡን ፍላጎትና የሥራውን ፍጥነት ማጣጣም እንደሚገባውም ገልጸዋል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ እንደተናገሩት፤ ኮሚሽኑ በእስካሁን ሂደቱ እያከናወነ ያለው ተግባር አበረታች ሲሆን፤ የዝግጅት ሂደቱ ከውጤቱ ጋር እኩል ፋይዳ ያለው በመሆኑ በፍኖተ ካርታ የተመራ እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በአጀንዳ ልየታ ላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማሳተፍ፣ የተግባቦት ፖሊሲና ሙዳየ ቃላትን ማዘጋጀት እንደሚገባም አቶ ክርስቲያን ጠቁመዋል።ከዚህ አኳያ ኮሚሽነሮቹ የትውልድና የአገር አደራ እንዳለባቸው አውቀው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው መክረዋል።

የምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ፤ የኮሚሽኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ እንዳለ ጠቅሰው፤ የአሠራር ሥርዓትን መዘርጋትና ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት፣ የባለሙያዎችና አማካሪ ቡድን ማደራጀት በቀጣይ ትኩረት ሊሰጥባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

የኮሚሽኑ ዋና ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ የተግባርና እቅድ ዘገባውን ሲያቀርቡ፤ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፣ ልዩነትን በውይይት የመፍታት ፍላጎት፣ የመንግሥትና የሕዝቡ ድጋፍ እንዲሁም ለኮሚሽኑ የተሰጠው ሙሉ ነጻነት ምክክሩን ለማካሄድ መልካም አጋጣሚዎች እንደሆነ ገልጸዋል።

በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የኮሚሽነሮች ትውውቅና የቡድን ግንባታ ማከናወን፣ መመስረቻ አዋጁን መረዳት፣ አባላቱን በኮሚቴዎች በማደራጀት ወቅታዊ ተግባራትን ማከናወን ከተሠሩ ሥራዎች መካካል እንደሆነ ጠቅሰዋል።የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ ከተለያዩ አካላት ጋር የመወያየትና ልምድ የመጋራት ሥራዎች እንደተከናወኑም አንስተዋል። በቀጣይም በተሰጠው የሀሳብ ግብዓት መሠረት በሰከነ መልኩ ሂደቱን እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

# ‹‹የረመዳን ወር ቀሪ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ረመዳን መተዛዘኛ፣ መተሳሰቢያና ልዩ ስጦታ የሚገኝበት ወር ነው፡፡ የመጀመሪያው 10 ቀናት የእምነት ቀናት ናቸው፡፡ ቀጣይ እስከ 20 ቀናት ያሉት ደግሞ ከፈጣሪ ምሕረት የሚገኝበት፣ መልካምነት የሚንጸባረቅበት ጊዜ ነው ብለዋል፡፡

በረመዳን ወር ሙስሊሞች የሚተባበሩበት፣ የሚተሳሰቡበትና የሚረዳዱበት ወቅት ነው፡፡ ምስኪኖች ረመዳን ቀለባችንን ይዞ ይመጣል በሚል የሚናፍቁበትና የሚደሰቱበት ወር ነው፡፡ አማኙም በመስጠትና በመደሰት የሚያሳልፍበት ወቅት ነው ብለዋል፡፡

ረመዳንን ለመጾምም ሰላም ያስፈልጋል፡፡ የሃይማኖትን ሕግ ለማንበብ፣ ቁርዓን ለመቅራት ሌላው አማኝም በእምነቱ የሚቀበለውን መጻሕፍት መመሪያ ማንበብና ማምለክ የሚችለው ሰላም ሲሰፍን ነው፡፡ የእምነት ነጸብራቆች ውብ የሚሆኑት ሰላም ሲኖር መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

ሰላም እንዲሰፍን ጸሎት ማድረግ ይገባል ያሉት ሼህ መሐመድ፤ በሃገር ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩ ችግሮችን ፈጣሪ እንዲያስቆም አማኞች በቀሪ የረመዳን ወቅት ዱአ በማድረግ ማሳለፍ እንደሚገባቸውም አመልክተዋል፡፡

ለሰላም መስፈን ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ለሚሞቱ፣ ከቀዬአቸው ለሚፈናቀሉ ወገኖች የሚያዝኑትና የሚሰቃዩት የራሳችን ወገኖች መሆናቸውን መረዳት አለባቸው፡፡ ከዚህ ድርጊት ተመልሰው፣ ከፈጣሪያቸው ታርቀው ለሰላም እንዲሰለፉ ፈጣሪ ልብ እና ቀልብ ይስጣቸው፡፡

በመጥፎ ድርጊት የተሰለፉ መጥፎ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ የሚቀጥፉት፣ የሚያሰቃዩት የሰውን ልጅ ነው፡፡ የሚያወድሙትም የሰውን ንብረት መሆኑን በመገንዘብ ከዚህ ድርጊት መመለስ እንዳለባቸው መክረዋል፡፡ ‹‹ድርጊቱን እንዲተውት በፈጣሪ ስም እማጸናቸዋለሁ፡፡ ጥሩ ነገር ማየት የሚቻለውም ይሄንን በማቆም ነው›› ብለዋል ሼህ መሐመድ፡፡

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን ለሰላም፣ ለሰዎች መቀራረብና አንድነት እንዲኖር ዋጋ መስጠት አለባቸው፡፡ ይህ እንዳይሆን የሚፈልግ የበጎ ነገር ተቃራኒ የሆነ ሰው በፈጣሪም በሰውም ዘንድ የተወገዘ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ መተባበር፣ መደማመጥ እና አንድነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ መሪዎች ለበታቾቻቸው ማዘን ይኖርባቸዋል፡፡ የበታቾቻቸውንም ማዳመጥ ይገባቸዋል፡፡ ሰው እንዳይበደል መቆርቆር አለባቸው፡፡ ለሕይወቱ፣ ለንብረቱ ዋስትና መስጠት እንደሚገባቸውም ሼህ መሐመድ ጠቁመዋል፡፡

ተመሪዎችም መሪዎቻቸውን ማክበር፣ መከተል፣ ማዳመጥና መረዳት እንደሚገባቸው፣ ሕዝቦችም ለመሪዎቻቸው ተመቺ መሆን እንዳለባቸው በመጠቆምም፤ ይህንን ማድረግ ከተቻለ በአገር አቀፍ የሚታየው ውስብስብ ችግርና መገፋፋትን ማስቆም እንደሚቻል፣ ካንድ አቅጣጫ እንዲቆም መፈለግ አግባብ አለመሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ደግ ነገር ካንድ አቅጣጫ ይመጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ደግን ነገር ለማስገኘት ሁሉም ሰው ርብርብ ማድረግ አለበት፡፡ ሁሉም ለሰላም፣ ለአንድነት፣ ለእድገት መሰለፍ ይጠበቅበታል፡፡ ለአገር እድገት የበኩሉን ሚና መወጣት አለበትም ነው ያሉት፡፡

ክፉን ነገር በማስወገድ መልካም ነገር እንዲሆን መመኘትና መጸለይ ይገባል ያሉት ሼህ መሐመድ፤ የሃይማኖት ሕግ በቀልን አይፈቅድም፡፡ ሃይማኖተኛም አይበቀልም፡፡ የበቀል አሠራርን ማስቆም፤ መበቃቀልን፣ መደማማትን፣ መኮራረፍን፣ መገፋፋትን ማስቀረት እንደሚያስፈልግም መክረዋል፡፡

ፈጣሪን የሚያስከፋ፤ ሕዝብም የሚጠላው ድርጊት በመሆኑ ይህንን አይነት ድርጊት ማቆም ይገባል፡፡ መልካም መሥራት፣ ለሰላም መሰለፍ፣ ለአንድነት መቆም እንደሚገባም አመልክተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በርክክቡ ላይ እንደተናገሩት ፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በተቋሙ ስር በተለያየ ጊዜ ሲጽፉ በነበሩ ደራስያን ስም አምስት ሺህ መጽሐፍትን በአምስት ቀን ለማሰባሰብ የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርግ ቆይቷል። ዓላማውን የተረዱ ጋዜጠኞች፣ የጥበብ ወዳጆች ከአዲስ አበባና ከተለያዩ ከተሞች መጽሐፍቶቻቸውን አስረክበዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ለ81 ዓመታት ሕዝብን ሲያስተምር የቆየው አንጋፋው የሚዲያ ተቋም የጀመረውን መጽሐፍት የማሰባሰብ ጥረት ይቀጥላል ያሉት አቶ ጌትነት፤ “በዕድሜ ልክ በሚል ስያሜ፤ የ81 ዓመታት የየዓመቱ 100 ምርጥ መጽሐፍት” በተሰኘ መርሐግብር ተመሳሳይ የመጽሐፍ የማሰባሰብ ሥራ እንደሚከናወን ገልጸዋል።

አብርኆት ምቹ የማንበቢያና ዕውቀት መገብያ ስፍራ መሆኑን አይተናል። ዕውቀት እንዲስፋፋ በተለያዩ ሥፍራዎች ላይ መጽሐፍትንና መጽሐፍት ቤቶችን ማስፋፋት ያስፈልጋል። እኛም ለአንባብያን የሚሆኑ መጽሐፍትን በማሰባሰብ ለማበርከት ስንነሳ አገር ለመገንባት ወሳኝ የሆነው ዕውቀት እንዲስፋፋ በማሰብ ነው፤ ይህ ጥረታችንም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል። ከሃገር አቀፉ የአንድ ሚሊዮን መጽሐፍት የማሰባሰብ ጥረት ጋር በተያያዘም ተቋሙ የሚያከናውናቸው ሰፋፊ ሥራዎች እንደሚኖሩ ጠቁመዋል።

በመጽሐፍ ርክክቡ ወቅት ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት እንዳስታወቁት፤ በሃገር አቀፍ ደረጃ ከሚያዚያ 28 ቀን እስከ ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ አንድ ሚሊዮን መፅሐፍትን ለአብርኆት ቤተመፅሐፍት ለማሰባሰብ ዝግጅት ተደርጓል።

መጽሐፍት ዕውቀትና ስልጣኔን ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ ወሳኝ ናቸው። የሃገራችንን ችግሮች መቅረፍ ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ ዕውቀት ነው። በዚህ ረገድ የአብርኆት ቤተመጽሐፍት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፤ የቤተመጽሐፍቱ ዓላማም የዕውቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል ነው ብለዋል።

ከምግብ እጥረት እኩል በዚህች ሃገር ችግር እየፈጠረ ያለው የዕውቀት እጥረት ነው ያሉት ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል፤ ለዚህ የሚመጥን የመጽሐፍትና የቤተመጽሐፍት አቅርቦት በየአካባቢው ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል። የዕውቀት እጥረት ልክ እንደምግብ እጥረት ሁሉ መፍትሔ ያሻዋል። የምግብ እጥረቱን በቫይታሚንና በፕሮቲንም መቅረፍ እንደሚቻው ሁሉ በሃገር ላይ ችግር እየፈጠረ ያለውን የዕውቀት ችግር ለመቅረፍ ደግሞ መጽሐፍት ወሳኝ ናቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በተቋሙ በሰሩ አንጋፋ ደራስያን ስም መጽሐፍትን አሰባስቦ ለአብርኆት ማስረከቡ የሚያስመሰግነው መሆኑን ጠቁመዋል።የሃገራችን ሚዲያዎች ሰዎች መጽሐፍትን እንዲያሰባስቡና እንዴት መሰብሰብ እንደሚችል እያስተማሩ ያሉበት መንገድ የሚደነቅ ነው። በተመሳሳይ በየመሥሪያ ቤቱና በየቤቱ የተቀመጡ መጽሐፍትን ወደቤተመጽሐፍት ማምጣት ያስፈልጋል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና በበኩላቸው፤ አብርኆት ቤተመጽሐፍትን በየቀኑም ከሶስት እስከ አምስት ሺህ ሰዎች ለንባብ እየጎበኙት መሆኑን ገልጸዋው፤ ይህም በአገራችን ያለው የቤተመጽሐፍትና የመጽሐፍት እጥረት ከፍተኛ መሆኑ ያሳያል። ሕዝብም ማንበብ ምን ያክል ፍላጎቱ እንደጨመረ ያመላክታል ሲሉ ተናግረዋል። በመሆኑም ከሕዝቡ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን የንባብ ባህልን ለማዳበር እንደአብርኆት ያሉ ቤተመጽሐፍትን በየክፍለ ከተማው መገንባት ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊዮን መጽሐፍትን ለማሰባሰብ የተያዘው ዕቅድም የቤተመጽሐፍቱን አቅም በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ተናግረዋል። አብርኆት ቤተመጽሐፍት አራት ሚሊዮን መጽሐፍት የመያዝ አቅም እንዳለው ገልጸው፤ በመሆኑም ቤተመጽሐፍቱ ውስጥ ቢያንስ ሁለት ኮፒ ያላቸው ሁለት ሚሊዮን መጽሐፍት ያስፈልጋሉ ሲሉ ጠቁመዋል።

በዚህ ረገድ የተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት መጽሐፍት በማሰባሰብ ረገድ እያደረጉ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም አምስት ሺህ መጽሐፍትን መለገሱ በሂደቱ አርዓያ መሆኑን ያሳያል ብለዋል። በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊዮን መጽሐፍትን ለማሰባሰብ በሚደረገው ጥረት ዜጎች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።



ዶክተር ሂሩት ካሳው

# ለኢድ በዓል ወደአገራቸው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚሆን ጥሪት ይዘው እንደሚመጡ ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ ለተለያዩ የንባብ ተቋማት የሚውሉ መጽሐፍትን ይዘው ቢመጡ ለትውልዱ ዕውቀት ማደግ የተሻለ አበርክቶ መጫወት ይችላሉ ብለዋል።

መጽሐፍ ዕውቀት ለመገብየት አይነተኛ መንገድ ነው፤ ይህንን ዕውነት መሠረት አድርገው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ወደአገራቸው በሚመጡበት ወቅት ያላቸውን የጽሑፍ ሀብቶች ይዘው ቢመጡ ለአገር ትልቅ አቅም እንደሚሆን ተናግረዋል።

እንደአብርኆት ቤተመጽሐፍት ያሉ በርካታ ወጣቶችን ማስተናገድ የሚችሉ ማንበቢያ ስፍራዎች አሉን ፤ እነዚህን ተቋማት ደግሞ በመጽሐፍት ማደራጀት የሁሉም ኃላፊነት ነው ብለዋል።

በዚህ ረገድ ከውጭ አገራት የሚመጡ ዜጎች የቻሉትን ያክል መጽሐፍትን ይዘው ቢመጡ ለወገናቸው የሚጠቅም ሥራ ማከናወን እንደሚችሉ አስታውቀዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚያዚያ መጨረሻ እስከ ግንቦት ወር ለሚከናወነው የአንድ ሚሊዮን መጽሐፍት ማሰባሰብ ዘመቻ ከወዲሁ ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

በአገር ውስጥ ያሉ ተቋማትና ግለሰቦች መጽሐፍቱን በማሰባሰብ ረገድ ከሚያደርጉት ጥረት ባለፈ ዲያስፖራው ማኅበረሰብ የበኩሉን ሚና መጫወት ከቻለ የተሻለ ውጤት እንደሚገኝም አስረድተዋል።

ዲያስፖራው ማኅበረሰብ ወደአገር ውስጥ ይዟቸው እንዲመጡ የሚጠበቁት መጽሐፍት ትውልድ በስነምግባርና በዕውቀት ለመቅረጽ የሚረዱና ትምህርትን ለማስፋፋት የሚያግዙ መሆን እንዳለባቸው የጠቆሙት ዶክተር ሂሩት፤ በዚህ ረገድ በቀጣይ በርካታ መጽሐፍትን ከኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንጠብቃለን ብለዋል።

ከዚህ ቀደም በእንግሊዝ ሃገር በትምህርት ላይ የምትገኘው ወጣት አምስት ሺህ 200 መጽሐፍትን ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት ማስረከቧ ይታወሳል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ተገኝተው ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት መጽሐፍ ለሚለግሱ ግለሰቦች ምስጋናዬ የላቀ ነው ብለው ነበር።

በእንግሊዝ ሃገር በትምህርት ላይ የምትገኘው ወጣት ቤተልሔም ሰሎሞን አምስት ሺህ 200 መጻሕፍት ከእንግሊዝ አምጥታ ማስረከቧ ለሌሎች አርዓያ እንደሚሆን መናገራቸው ይታወሳል።

በወቅቱም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አንድ ዐቢይ ኮሚቴ የተዋቀረ መሆኑን ጠቁመው፤ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ወገኖች የመጽሐፍት ልገሳ ለማድረግ እንዲዘጋጁና፣ ለትውልድም የሚውል ዕውቀት እንዲለግሱ ጥሪ ማቅረባቸው የሚታወስ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ አሸባሪ ቡድን ነው!

ሕወሓት የቆምኩት ለትግራይ ሕዝብ ነው፤ የትግራይን ሕዝብ ነጻ አወጣለሁ እያለ በተደጋጋሚ ጊዜ ተደምጧል፤ ይሄንኑ ዲስኩሩን ላለፉት 50 እና ከዛም በላይ ለሆኑ ዓመታት ሕዝቡን ሲሞላ ቆይቷል። አሁንም ቀጥሏል።

ይሁን እንጂ አንድም ጊዜ የትግራይ ሕዝብ ከጦርነት ወጥቶ የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖር ዕድል አልሰጠውም፤ አንድም ጊዜ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆን አላስቻለውም። ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በሰላምና በፍቅር እንዲኖር ዕድል አልፈጠረለትም። ይልቁንም ለፕሮፖጋንዳውና ስውር አጀንዳው መጠቀሚያ ሲያደርገው ኖሯል።

የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር ተሳስቦና ተከባብሮ እንዳይኖር በተለያየ አቅጣጫ ጠላት ሲፈጥርለት፤ ልጆቹን ለትምህርት ሳይሆን ለጦርነት ሲያስገብረው ቆይቷል። አብዛኛው ወላጅ ጥሮ ግሮ ለመኖር ተገዷል። እስካሁንም ከልፋቱ ሳይወጣ ጦርነት ለሚጎስሙለት ጥቂቶች አናናሪ ሆኗል። ዛሬም የፖለቲካ ጨዋታው ከዚሁ ቅኝት የወጣ አልሆነም። ጥቂቶች ኢኮኖሚያቸውን እያደለቡና በስሙ እየነገዱ የራሳቸውን የተንሰራፋ ሀብት ማካበት ቀጥለዋል። የትግራይ ልጆች ትምህርት እየናፈቃቸው የእነሱ ልጆች ከሃገር ወጥተው በተቀናጣ ኑሮ በቅንጡ ትምህርት ተቋማት በመማር ላይ ናቸው።

ይሄ ብቻ አይደለም፤ የትግራይ ሕዝብ በረሀብ እየታመሰ እነሱ በስሙ የሚመጣን ርዳታ ለፖለቲካ ጨዋታቸው ሲያውሉት በተደጋጋሚ ታይቷል። ሕወሓት ከጥንት ታሪኩ ለተራበ ሕዝብ የመጣን የሰብዓዊ እርዳታ በመሸጥና የጦር መሣሪያ በመግዛት ይቅር የማይባል መጥፎ የታሪክ አሻራን ያስቀመጠ አሸባሪ ቡድንም ነው።

ይሄ በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚሰራው ደባ ዛሬ ብቻም ሳይሆን አስቀድሞም የፖለቲካ መጠቀሚያ ሲያደርገው እንደነበር የሚያስታውሰን ነው። አሁን የሚደግመው የለመደውን ተመሳሳይ ጨዋታውን ነው። ዛሬም የትግራይን ሕዝብ ሕይወት እየታደገ ሳይሆን ልጆቹን ለጦርነት እያስገበረ ነው። ዕድሜያቸው ለውትድርና ያልደረሱ፣ በቂ ወታደራዊ ስልጠና ያላገኙ ታዳጊና ወጣቶችን በመመልመል ለጦርነት እየገበረ ይገኛል። በጠላት ተከበሀል እያለም ከወንድም እህቱ ጋር ለማራራቅ በአማራ፣ በአፋር እና ከኤርትራ ሕዝብ ጋር ጠላት በመፍጠር ዛሬም የመኖር ህልሙን፣ የነገነ ተስፋውን እያጨናገፈው ይገኛል። ለልማት እና ለሰላም ከማሰብ ይልቅ ጦርነትን እየናፈቀና ጸብ እየደገሰ ሕዝቡን ለከፋ ስቃይ በመዳረግ ላይ ነው። ለትግራይ ሕዝብ ቆሜያለሁ እያለ ተግባሩን ግን በተቃራኒው ነው።

ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ አለመቆሙን ለማንሳት የቅርቡን ማስታወስ ብቻ በቂ ነው። የትግራይ ሕዝብ ተራበ ፣ የእርዳታ ማስገቢያ ኮሪደር ይከፈትልን ፣ መድኃኒት የለም፣ እያለ ይደስኩር እንጂ በተግባር ግን እያደረገ ያለው ለሰብዓዊ እርዳታ የመጣውን እህል እና አልሚ ምግብ ሳይቀር ለሠራዊቱ ምግብነት ሲያውለው ነው። የዓለም ጤና ድርጅት ያስገባውን መድኃኒት ለሆስፒታሎች ከማከፋፈልና ሕሙማኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ ይልቅ ለጦር ካምፖች በማስገባት እንዲሁም የግል ፋርማሲዎችን በመክፈት የገቢ ምንጭ እያደረገው ይገኛል። እነዚህና ሌሎች በርካታ የጭካኔ ተግባራቱ ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ አሳቢና ወዳጅ ሳይሆን ጠላትነቱን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው። ለትግራይ ሕዝብ እንባ አባሽ ሳይሆን እንባ አፍሳሽ መሆኑን ያስመሰክራል። አሁንም በአንድ በኩል በረሀብ ፣ በመድኃኒት እጥረት እና ማጣት የሚሞተው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጦርነት ልጁን የሚገብረው የትግራይ ሕዝብ ነው።

የዓለም ጤና ድርጅት በርካታ የመድኃኒት ርዳታ አድርጓል። ሕወሓት አፋርና አማራ ክልሎች በገባበት ወቅት ለአንድ ዓመት ሊያቆየው የሚችለውን መድኃኒት ዘርፎ መውሰዱ ይታወሳል። አሁንም ድረስ ከሰብዓዊ እርዳታ ጋር የመድኃኒት እርዳታም እየገባ ይገኛል። ይሁን እንጂ የትግራይ ሕዝብ በመድኃኒት እጦት እየሞተና እየተሰቃየ ነው።

በአጠቃላይ ሕወሓት ከአጠቃላይ ባህሪው አንጻር ሲመዘን የትግራይ ሕዝብ ጠላት እንጂ አንድም ጊዜ ወዳጅ ሆኖ አያውቅም። አሁንም እናት መከራዋን አይታ ያሳደገቻቸውን ከጦርነቱ የተረፉ ልጆቿን ሳትወድ በግድ ለጦርነት እየገበረች ትገኛለች ። ለሞቱት ልጆቻ እርሟን ሳታወጣ አንጀቷ አርሮ የመከራን ዳገት እየገፋች ነው።

እናም ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ ለዘመናት ጠላት እንጂ አንዴም ወዳጅ ሆኖ እንደማያውቅና አሁንም መሠረታዊ ጠላታቸው መሆኑን በተግባሩና በሚፈጽመው አረመኔያዊ ሥራው እያስመሰከረ ይገኛል። ስለሆነም አሁንም ሕወሓት ወዳጁ ሳይሆን ጠላቱ፤ አሳቢው ሳይሆን ጎጂው መሆኑን ሊረዳና ጠላትነቱን አውቆም ሊታገለው ይገባል!


እፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# "ወሬ" - ሌላው የዋጋ ንረት ሳቦታጅ

**ሰላማዊት ውቤ**

አባቶቻችን ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ይበልጣል የሚሉት ተረት አላቸው፡፡ ምክንያቱም፣ ወሬ ለማፍረስም ሆነ ለመገንባት ትልቅ አቅም ያለው በቀላሉ የማይታይ፤ ትንሹን ጉዳይ ትልቅ አድርጎ በማግዘፍ ትኩረት የመሳብ፤ የብዙዎቹን ኑሮና ሰላም የማናጋት እንዲሁም ትዳር ከማፍረስና ቤተሰብ ከመበተን አልፎ ተርፎ በሕዝቦች መካከል ጥላቻ በመዝራት፣ በቀል በማትረፍና ቂምና ስጋት በመቀስቀስም የሚወዳደረው የለም፡፡ አስፈላጊ ከሆነ አቅሙ የብዙዎችን ቤት ብቻ ሳይሆን ሃገርም ለማፍረስ የሚያንስ አለመሆኑን ብዙ ማስረጃዎችን ዋቢ አድርጎ ጥንካሬውን መናገር ይቻላል፡፡የሊቢያው መሪ ጋዳፊን መጠነ ሰፊ የሕዝብ አመጽ በማስነሳት ግብዓተ መሬታቸውን ለማፋጠን መብቃቱ፤ የሱዳን መሪ የነበሩትን አልበሽርን መንበረ ስልጣን ነቅንቆ ለሥር መዳረጉን እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡

ስለ ወሬ አቅምና ጉልበት ይሄን ካልኩ ዘንዳ፤ ለዛሬው ላነሳ ወደ ወደድሁት ጉዳይ ልመለስ፡፡ ለዛሬ አጀንዳ ማድረግ የፈለግኩት ወሬ ባሳለፍነው ትንሳኤ በዓል ገበያ ላይ ለመፍጠር ታስቦ የነበረውን ሳቦታጅ ነው፡፡ ሳቦታጁን መዝራት የጀመረው ገና የሁዳዴ ጾም ከመግባቱ አንስቶ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ ጎመንን እንደ አንድ ማሳያ ብናነሳ፤ ጾሙ የገባ ሰሞን 10 ብር የነበረው ጎመን 20 ብር እንደገባ በሰፊው መወራት ጀመረ፡፡ ብዙ ሰዎች በዚህ ወሬ ተናጡ፡፡ ስጋት አድሮባቸው ጎመን ለመጠየቅም የፈሩ ነበሩ፡፡ ጎመን 20 ብር ሆነ እንዴ? ብለው ለመጠየቅ የደፈሩ ሰዎችም እራሳቸው በወሰኑት ዋጋ ብልጦች ነጋዴዎች ሆነ አዎን ብለው የ10 ብሩን ጎመን 20 ብር ሲሸጡላቸው ተስተውሏል፡፡

በወቅቱ የጎመን ዋጋ 20 ብር የሆነው በወሬ እንጂ በነጋዴው ውሳኔና አምራቹ ዋጋ በመጨመሩ አልነበረም፡፡ ይሄን የሁዳዴ ጾም የገባ ሰሞን በወሬ ደረጃ የተናፈሰውን ሰምቶ ሊገበይ በሄደው በራሱ በሸማቹ ውሳኔ በ20 ብር የተሸጠውን ጎመን፤ በተመሳሳይ መጠን ብዙ ጎመን ነጋዴዎች ዘንድ እንደቀድሞው የጎመን ዋጋ በ10 ብር ሲሸጥ እንደነበረም መግለጹ ተገቢነት አለው፡ ይህ የሚያሳየው ሁሉም የአፉንና የጆሮውን ፍሬ ማግኘቱን፤ በ20 ብር ሆነ ወሬ የተነዳው በ20 ብር ሲበላ፤ የወሬውን ረብ የለሽ የተገነዘበው ደግሞ በ10 ብር ሸምቶ መመገቡን ነው፡፡ ስለዚህ በወቅቱ የጎመን ዋጋ አንዳንድ ነጋዴዎች ዘንድ በእጥፍ በማደግ 20 ብር የገባው «በለፈለፉ በአፍ ይጠፉ» እንዲሉ፣ የሚናፈሰውን ወሬ ተከትሎ ጎመን ነጋዴ ጋር ሄዶ ጎመን 20 ብር መግባቱን በጠየቀ ጎመን ሸማች ውሳኔ ጭምር መሆኑን መታዘብ ችያለሁ፡፡

በጎመን የጀመረው የዋጋ ንረት የሁዳዴው ጾም እየገፋ ሲመጣ በዚሁ በወሬ እየተገፋ መጥቶ ቀድሞውንም «እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ» እንዲሉ፣ በየጊዜው እየናረ የመጣውን የዘይት ዋጋ በፍጥነት የብዙዎቻችን የወር ደሞዝ የማይገዛውና የዕለት ምግብ ሳይሆን የቅንጦት ፍጆታ አድርጎት አረፈ፡፡ እኔ እንደታዘብኩት የዚህ የዘይት ዋጋም ቢሆን በፍጥነት ተመንድጎ እዚህ የቅንጦት ፍጆታዎች ደረጃ መድረስ የቻለው የምርቱ ዋጋ ከቦታው ሲመጣ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ጨምሮ ሳይሆን እንደተለመደውና እንደጎመኑ ሁሉ በወሬ ተገፍቶ ነበር፡፡ «ማየት ማመን ነው» እንዲሉ መነን አካባቢ 110 ብር ተብሎ የነበረ ለአንድ ሊትር ትንሽ ቅር የሚለው የሱፍ ዘይት አሥር ባልሞላ ደቂቃ ውስጥ 185 ብር ሲሸጥ መታዘብ ችያለሁ፡፡ በተመሳሳይ በዚሁ ደቂቃ ውስጥ 160 ብር ተብሎ የነበረ አንድ ሊትሩ የዚሁ የሱፍ ዘይት ዋጋ ደግሞ በወሬ ግፊት ብቻ 200 ብር መግባቱንም አይቻለሁ፡፡

በዚህ መልኩ በወሬ ሲገፋ የመጣ ዘይት ዋጋ ባሳለፍነው የትንሳኤ በዓል ዕድሜ ለወረኞችና ከ500 እስከ 700 ብር የነበረው ባለ አምስት ሊትር ዘይት ዋጋ እስከ 1ሺህ 200 ብር ለመሸጥ በቅቷል፡፡እንዲህም ሆኖ በወሬ ባልተሸነፉ ብዙዎቹ ባለመደብሮች ጋር ደግሞ 920 ብር ተሸጧል፡፡ ባለ አንዱ ሊትር የዚሁ የሱፍ ዘይት ከ195 ብር እስከ 250 ብር በመሸጡ ሕብረተሰቡ በወሬ እየተገፋ በተቆለለው የዘይትም ሆነ ሌሎች ምርቶች ዋጋ ምክንያት በዓልን ለማክበርም ተገድዷል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ገበያውን ለማረጋጋት በተደረገው ጥረትና በተወሰኑ ሸቀጦች ላይ አቅርቦት እንዲጨምርና በማኅበራትና ሌሎች ባለድርሻዎች በኩል እንዲቀርብ መደረጉ በተወሰነ መልኩ ለበዓል ገበያው መረጋጋት ማበርከቱ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ለዚሁ በዓል በዋንኛነት አስፈላጊ የሆኑ ሽንኩርት እና ዶሮም ከዚሁ ከገበያ የወሬ ሳቦታጅ ሰለባነት አልዳኑም ነበር፡፡ ሰሞነ ሕማማት ለመግባት ሳምንት ሲቀረው በወሬ እየተገፋ 40 ብር የገባው ቀይ ሽንኩርት ሰሞነ ሕማማት ሲገባ በፍጥነት እስከ 50 ብር መግባቱ ተሰማ፡፡ በተለይ ሃገር በቀል ዝርያ መሆኑ የሚነገርለት የሀበሻ ቀይ ሽንኩርት ዋጋ 70 ብር መድረሱም ተነገረ፡፡ ይሄም በዋጋ ንረት ብዛት የመግዛት አቅሙ እየተዳከመና የትንሳኤን በዓል የማክበር ተስፋው እየተሸረሸረ የመጣውን ኅብረተሰብ በስጋት ሲንጠው ቆየ፡፡ ነገር ግን እንደ ተፈራው የገበያ ሳቦታጅ ወሬ ሚርቱ ሳይዝለት ቀርቶ እስከ ትንሳኤ በዓል ዋዜማ የአንድ ኪሎ ሽንኩርት ዋጋ እስከ 35 ብር በማሽቆልቆል ወርዶ ኅብረተሰቡ ሽንኩርት ሸምቶ በዓሉን ማክበር ቻለ፡፡

የአንድ ዶሮ ዋጋ አንድ ሺህ ብር እና ከዛም በላይ የመግባቱ ወሬ መናፈስ የጀመረውም በሰሞነ ሕማማቱ ወቅት ነበር፡፡ወሬው በኅብረተሰቡ ዘንድ የዶሮ እጥረት ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋትም ፈጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም በዘንድሮ ትንሳኤ በዓል እንደ ዕድል ሆኖ የዚሁ የገበያ ሳቦታጅ ወሬ ሚርቱ ሳይዝለት ቀርቶ የሀበሻውም ሆነ የፈረንጁ ዶሮ ዋጋው በፍፁም እንደ ታሰበው ሊጋነን አልቻለም፡፡እስከ በዓሉ ዋዜማ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በየመኪናው ላይ የትኞቹም አካባቢዎች አንድ ዶሮ እስከ 400 ብር ሲሸጥ ውሏል፡፡ ታርዶ የተበለተውም ቢሆን በየሱፐር ማርኬቶቹ በተለይም አራት ኪሎ ባሉት ሱፐር ማርኬቶች በተመሳሳይ ዋጋና እንደ ልብ መሸጥ በመቻሉ የገበያ ሳቦታጅ ወሬው ሚርት ሳይዝ ቀርቷል፡፡

ይህ እውነት የሚያስረዳን ደግሞ በአገራችን ለሚስተዋለው የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ችግር እንደ ምክንያት ከሚነሱ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ ከውጪ ምንዛሪ ችግር፣ ከደላላ፣ ከነጋዴ ሥነምግባር፣ ከገበያ ቁጥጥርና ክትትል መላላት፣ ከሕግ ማስከበርና ተያያዥ ጉዳዮች ባሻገር፤ በወሬ ደረጃ የሚነገረው የሸቀጦች ዋጋን አንሮ የመሳል አካሄድ አንድ መንስኤ መሆኑን ነው፡፡ ይህ በወሬ ላይ የተመሠረተ ዋጋን የማናር አካሄድም አሉባልታውን ለተከተለ የሚሠራ፤ ወሬን አጣርቶ ለሚራመድ የማይሠራ መሆኑን መታዘብ ይቻላል፡፡ በትንሳኤው ገበያ የታየውም ይሄው ነው፡፡ ሆኖም ወሬ አንዱ የዋጋ ንረት መፍጠሪያ ሳቦታጅ መሆኑን ተገንዝበን ልንጠነቀቅ፤ በሐሰት ወሬ ላይ ተመሥርቶ ከሚፈጠር የዋጋ ንረት ለመጠበቅም ሐሰትን በእውነት ልናከሽፍም ይገባል፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

# በመኪና ማጠቢያ ስፍራ ላይ የተነሳው እሰጥ አገባ

**ሙሉቀን ታደገ**

የዛሬው የፍረዱኝ ዝግጅታችን ወደ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ልዩ ስሙ ድል በር ተብሎ ወደ ሚጠራው አካባቢ ይወስደናል።አቤቱታ አቅራቢው አቶ ስንታየሁ አየለ ይባላሉ ።በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ድል በር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ሲሆኑ ፤ የመኪና እጥበት በማከናወን ኑሮአቸውን የሚመሩ ግለሰብ ናቸው።

የመኪና እጥበት የሚያከናውኑበትን ቦታ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ እንደያዙት አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ።ይሁን እንጂ መኪና እያጠቡ ቤተሰባቸውን ሲያስተዳድሩበት የነበረውን ቦታ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ ሰባት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ውርጭ ፣ ቁር እና ፀሐይ እየተፈራረቀባቸው ያለሙትን የመኪና ማጠቢያ ቦታ እንዲፈርስ በማድረግ ከስምንት ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመትን ንብረት ግማሹን በማውደም እና በማበላሸት ፤ ግማሹን ደግሞ በግብር ኃይል ጭኖ በመውሰድ ግፍ እንደሠሩባቸው ይገልጻሉ።

«የሕዝብን ችግር ይፈታሉ ተብለው በተቀመጡት የሥራ አስፈጻሚ ያልተገባ ተግባር ለከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ እና የስነ ልቦና ጫና ስለተዳረኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰብኝን በደል ተመልክቶ ይፍረደኝ!» ሲሉ አቶ ስንታየሁ አየለ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል።የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግራ እና ቀኙን በማየት መፍረድ ይችል ዘንድ ዝግጅት ክፍሉ የደረሰበትን ሙሉ የምርመራ ውጤቱን እነሆ ብለናል።መልካም ንባብ።

**ከአቤቱታ አቅራቢው አንደበት**

አሁን ላይ ውዝግብ የተነሳበት ቦታ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የመኪና እጥበት የሚያከናውኑበት እና ቤተሰባቸውንም ሲያስተዳድሩበት የቆየ እንደነበር አቤቱታ አቅራቢው ይገልጻሉ። መጀመሪያ ላይ ቦታው አግባብነት ባለው የመንግሥት አካል የተሰጣቸው አልነበረም ።ይሁን እንጂ መኪና የሚያጥቡበት ቦታ በግልጽ የአየር ካርታ ላይ ይታያል። በመሆኑም መንግሥት በ2006 ዓ.ም ከሰነድ አልባ ቦታዎች ጋር ተያይዞ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 07 ካቢኔ አባላት ተወያይተው እና ገምግመው በ2007 ዓ.ም ቦታው ካርታ እንዲሠራላቸው የሚል ውሳኔ አስተላለፉ።ከውሳኔ በኋላ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክፍለ ከተማ ባለሙያዎች ቦታውን ለመለካት እና ለመሸንሸን በማሰብ ካርታ እንዲሠራለት ወደተባለው ቦታ በማቅናት ቦታውን ለኩ ።የቦታው ስፋትም 886 ካሬ ሜትር ሆነ ።ነገር ግን ለአንድ ድርጅት መሰጠት የሚችለው ከ5 መቶ ካሬ ሜትር መብለጥ ስለሌለበት ለመኪና ማጣቢያ የሚሆን ከ5 መቶ ካሬ ሜትር ለክተው እና ሸንሽነው ሄዱ።የቦታውን ተከትሎ ካርታውን ለመውሰድ የክፍለ ከተማውን መሬት አስተዳደር መጠባበቅ ያዙ።

ይህ በእንዲህ እያለ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ የወጣበት ውሃን ሪሳይክል የሚያደርግ መሣሪያ በመኪና ማጠቢያ ቦታቸው ተከሉ።«ሪሳይክል »ማድረጊያው ማሽን አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለን ውሃ ለ37 ጊዜ መጠቀም የሚያስችል ነው ።

ከመኪና ማጠቢያው አጎራባች በአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን የሚተዳደረው ቦታ ይገኛል።ይህን ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን የሚተዳደረው ቦታ ሪሳይክል በሚደረገው ውሃ አጠቃላይ የሆነ ስነ ምህዳር ለችግር ያደርሳል በሚል እሳቤ የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽኑ የመኪና ማጠቢያው መሬት የኔ ነው የሚል ጥያቄ አነሳ።

ይህን ተከትሎ አቤቱታ አቅራቢው በአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ጋር ሪሳይክል የሚደረገውን ውሃ ጉዳት መጠን ለመገምገም ያስችል ዘንድ በየጊዜው የሚታደስ ውል ለመግባት ተገደደ።

ውሉ በሠራተኛ ሰውነት እና በመኪናዎች አካል ላይ እንዲሁም በአካባቢው አጠቃላይ ሁኔታ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ እየታየ እና ሪሳይክል የሚሆነውን ውሀ እየመረመሩ ፈቃዳችን እንዲታደስ የሚል ነው። ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ያለን ግንኙነት ይህ ነው ።

ይሁን እንጂ ከሰባት ዓመት በፊት የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽን መሬቱ የእኔ ነው በማለት ክስ ጀምሮ ነበር።በዚህ ክርክር መሬቱ የእነሱ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ተከራክረው የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽን መሸነፉን አቤቱታ አቅራቢው ይናገራሉ።በ2012 ዓ.ም የተወሰነው ውሳኔ መሬቱ የአቤቱታ አቅራቢው ስለመሆኑ እና የፍርድ ቤት ውሳኔ በእጃቸው እንደሚገኝም ይገልጻሉ ።

በክርክሩ ወቅት እና ከክርክሩ በኋላ የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽን ለንግድ እና ኢንዱስትሪ በጻፈው ደብዳቤ መሠረት የመኪና እጥበቱ ንግድ ፈቃዱ እንዳይታደስ ከለከለ።ለሰባት ዓመት ያህልም የንግድ ፈቃዱ ሳይታደስ እንዲቆይ ተደረገ።ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ደግሞ ንግድ ፈቃድ ሳይኖርህ መሥራት አትችልም ብሎ ከለከለ።በዚህም ሁከት ይወገድልኝ በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን እና የጉለሌ ክፍለ ከተማን የአካባቢ ጥበቃን ኮሚሽን እና የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት አስተዳደርን በአንድ ላይ አጣምረው ከሰሱ።በመጨረሻም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃን እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን የመኪና እጥበት የሚካሄድበትን ቦታ የአካባቢ ጥበቃ የማያስተዳድረው « ከግሪን ኤርያ» ውጪ መሆኑን መርምሮ ንግድ ፍቃዱን አድሱለት ብሎ ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጻፈ።

ከብዙ የይገባኛል ክርክር በኋላ የንግድ ፈቃዱ እንዲታደስ የሆነበት ዋናው ምክንያት የአዲስ አበባ ከተማ የተቀናጀ የመሬት አስተዳደር መረጃ ማዕከል ቦታው « ከግሪን ኤርያ» ውጪ መሆኑን በማመላከቱ ነው ።

የተቀናጀ የመሬት አስተዳደር ማዕከል የሰጠውን መረጃ ተከትሎ ከደን አስተዳደር ውጭ በመሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽን የመሬት ይገባኛል ክሱን ትቶት ነበር ።ሁከት ይወገድልኝ ፍርድ ከተፈረደ አራት ዓመቱ ነው ።

ነገር ግን በ18/4/2014 ዓ.ም የአላሰቡት ነገር ይገጥማቸዋል ።በሌሊት ከመኖሪያ ቤታቸው ተነስተው ወደ መኪና ማጠቢያ ቦታው ያመሩት አቤቱታ አቅራቢው የመሥሪያ ቦታቸው በሰዎች ተሞልቷል። ግማሾቹ የመኪና ማጠቢያ መሣሪያዎችን ይነቃቅላሉ።ግማሾቹ በግቢው የነበሩ የቤቶችን ጣሪያ ያፈርሳሉ።ከፊሉ ደግሞ የቡድን እና የግል የጦር መሣሪያ ይዘው ይታያሉ።

በሌሊት የመኪና ማጠቢያ ቦታቸውን የቡድን መሣሪያ በያዙ በርካታ የፌደራል ፖሊስ አባላት ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ በቁጥር ዘጠኝ እና በርካታ የደንብ ማስከበር ቡድን ተከቦ ሲመለከቱ አቤቱታ አቅራቢው መጀመሪያ ላይ ወቅቱ ሃገሪቱ በተለያዩ የጥፋት ቡድኖች የምትፈተንበት አደገኛ ጊዜ ስለነበር እና ኮማንድ ፖስትም የታወጀበት ወቅት ስለነበር እና የመኪና ማጠቢያው ከጫካ ስር እንደመሆኑ መጠን የጥፋት ኃይሎች በማጠቢያ ቦታ ተደብቀው የተገኙ መስሎአቸው እንደነበር ያስረዳሉ።


ነገር ግን ተጠግተው ጉዳዩን ባጣሩ ጊዜ የቡድን መሣሪያ የታጠቀው የፌደራል ፖሊስ አባላት ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ እና በርካታ የደንብ ማስከበር ቡድን በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 7 ሥራ አስፈጻሚ የሚመራ የመኪና ማጠቢያ ቦታቸውን የሚያፈርስ ግብረ ኃይል ነበር፡፡ግብረ ኃይሉም ብዛት ንብረት የያዘን ቤት ጣራ በማፍረስ የመኪና ማጠቢያ ቦታውን መውጫ እና መግቢያ ከጣራው ባፈረሱት ቆርቆሮ አጥር ሠርተው ዘጉ ።የሠሩትን አጥርም አሸጉ። የታሸገውን ቤት በራሳቸው ማስጠበቅ ሲገባቸው እነሱ አፍርሰው ሲያበቁ የፈረሰውን ቤት አቤቱታ አቅራቢውን ዘበኛ ቀጥሮ እንዲያስጠብቅ አደረጉ።

አቤቱታ አቅራቢው ለምን የመሥሪያ ቦታቸው እየፈረሰ እንዳለ የግብር ኃይሉን መሪ እና የወረዳ 7 ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት ወይዘሮ ደራርቱ አላናን ይጠይቃሉ።ወይዘሮ ደራርቱም መሬቱ የመንግሥት እንደሆነ እና ፍርድ ቤትም ይህንኑ ስላረጋገጠ ቦታውን ወደ መንግሥት ይዞታነት ለመመለስ የሚደረግ አስተዳደራዊ እርምጃ መሆኑን ይነግሯቸዋል።

ወረዳው ትክክለኛ የሕግ መሠረት አለን የሚል ከሆነ እና የመኪና ማጠቢያ ቦታው በሕገወጥ መንገድ የያዝነው መሆኑ ካረጋገጠ ሕገወጥ ስለመሆናችን ተነግሮን እና የወረዳው ማህተም ያረፈበት ቁጥር ያለው ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ሊሰጠን ይገባ ነበር ።ማህተምም ሆነ ቁጥር የሌለው ደብዳቤ እንኳን ባይሰጡን በቃል ማስጠንቀቂያ ሊሰጡን ይገባ ነበር ። ነገር ግን ምንም አይነት ማስጠንቀቂያ ባልተሰጠበት ሁኔታ በሃገሪቱ የታወጀውን የኮማንድ ፖስት ሽፋን በማድረግ የቡድን መሣሪያ በታጠቁ ኃይሎች ትብብር በብዙ ሺህ ገንዘብ ወጭ ተደርጎ የተገዙ ንብረቶች እንዲቃጠሉ እና ጉዳት እንዲደርስባቸው ተደርጓል ሲሉ አቤቱ አቅራቢው ይናገራሉ።

የፍርድ ቤት አፈጻጸም ነው እየሠራነው ያለው ካሉኝ በደብዳቤ በሰላሳ ደቂቃ ወይም በሰላሳ ቀን ልቀቁ ብሎ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።ግን ያን አላደረጉም ። ወረዳው እንደመከራከሪያ ያቀረበው የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሁከት የለም እንጂ የሚለው ቤቱን ሰብራችሁ እና ጣራውን ገንጥላችሁ አጥር በመሥራት አሽጉ አይልም።

ድርጅቱ በወረዳ ሥራ አስፈጻሚዎች ከመውደሙ በፊት 180 ቋሚ እና 20 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ነበሩት የሚሉት አቤቱታ አቅራቢው ፤ 180 የሚሆኑት ግብር እና የጡረታ ክፍያ ይከፍሉ የነበሩ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪም መሆናቸውን ይገልጻሉ ።


ባአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
Addis Ababa City Government
የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን
Environmental Protection & Green Development Commission
ቁጥር / Ref No 203/20-01/2793
ቀን / Date 9/8/2011

ለ አቶ ስንታየሁ አየለ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ለፃፉት አቤቱታ ምላሽ መስጠትን ይመለከታል፤

በጉለሌ ክ/ከተማ በወረዳ 7 ድል በር ወደ እንጦጦ በሚወስደው መንገድ ... [illegible] ... እንዲነሳልዎት 01/8/2011 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል።

ሆኖም መ/ቤታችን ... [illegible] ... (EIA) ... [illegible] ...

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 7 [illegible] ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ፍትህ ጽ/ቤት

011-6-46 38 43
011-6-46 38 44
011-8-33-25-11
Fax 251 11-6-46 38 41
Email addisepa25@gmail.com

**በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 7 ዋና ሥራ አስፈጻሚ ምላሽ**

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 7 ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ደራርቱ አሊቃ ይባላሉ።የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ከአቶ ስንታየሁ የመኪና ማጠቢያ ቦታ ጋር ተያይዞ ስለተወሰደው እርምጃ ሰነዶችን እና መመሪያዎችን እያጣቀሰ ከወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ደራረቱ አላና ጋር ሰፋ ያሉ ውይይቶችን እና ክርክሮችን አድርጓል።የተደረጉ ውይይቶችን እና ክርክሮችን በጥልቀት አንብቦ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ፍርድ ይስጥ ብለናል።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 7 ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑትን ወይዘሮ ደራርቱን ስለጉዳዩ ያውቁ እንደሆነ ጠየቀ።ዋና ሥራ አስፈጻሚዋም ስለጉዳዩ በጥልቀት እንደሚያውቁ ገልጸው፤ አቶ ስንታየሁ አየለ የተባሉት ግለሰብ አንድ መኪናን ለማጠብ የተጠቀሙበትን ውሃን መላልሶ በመጠቀም መኪናን ማጠብ እንደሚችሉ ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ፕሮፖዛል ያስገባሉ።በዚህም ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ከሚያስተዳድረው መሬት ሁለት መቶ ካሬ ሜትር የሚሆንን ቦታ በጊዜያዊነት ሰጥቶት እንዲሠሩ ተደርጎ ነበር ።በጊዜያዊነት ማለት ዛሬም ሆነ ነገ ልቀቅ ማለት እንደሚቻል ይታወቃል ።

ይሁን እንጂ ግለሰቡ በጊዜያዊነት ከተሰጠው ቦታ በተጨማሪ ያለ አግባብ መሬቱን በማስፋፋት ያዘ።የአካባቢ ጥበቃ ይህንንም ሕገወጥ መስፋፋት እየተመለከተም ቢሆን በጊዜያዊነት እየተዋዋለ የመኪና ማጠቡን ሥራ እንዲሠራ ፈቅዶለት ቆይቷል።

አቶ ስንታየሁ የተባለው ግለሰብ ከተዋዋለበት መሬት ውጭ በራሱ ፈቃድ የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቅ በሕገ ወጥ መልኩ 3274.6 ካሬ ሜትር ላይ አድርሶታል። መሬትን ሕገወጥነት እየወረረ ያለ አግባብ ይዞታውን ሲያስፋፋ ቆይቷል።

ይህ ሆኖ ሳለ የአካባቢ ጥበቃ ለምን ከተፈቀደልህ ውጭ ቦታ አስፋፍተህ ትይዛለህ ብሎ ሲጠይቀው እና የመንግሥትን መሬት ወደ ግሉ ለማዞር የወረዳ አመራሮችን በማጭበርበር ካርታ ፕሮሰስ ለማሠራት

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

ሲሞክር በመታወቁ እና ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ሲጠየቅ ግለሰቡ በራሱ ተነሳስቶ በ2011 ዓ.ም ፍርድ ቤት ሄዶ የአካባቢ ጥበቃን ከሰሰ።ክሱ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ነበር ።

ሁከት ይወገድልኝ የሚለውን እግድ ሲያመጣ እግዱን የጻፈው ፍርድ ቤት ስለሆነ እና ሕግ መከበር ስላለበት የፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ አቶ ስንታየሁ ሥራውን እየሠራበት ቆይቷል።በዚህም ክርክሩ እስከ ሰበር ሂዶ ነበር ።በፍርድ ቤት ክርክሩም የአካባቢ እንክብካቤ ኮሚሽን እንቅስቃሴ ሕግን ለማስከበር እንጂ ሁከት አይደለም ሲል በ2012 ዓ.ም 9ኛ ወር ውሳኔ አስተላልፏል ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚያዋ ያስረዳሉ ።

ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ሁከት ይወገድልኝ ብሎ መጠየቅ እና በፍርድ ቤት ሁከት የለም በመባሉ መሬቱ የአንተ ስላልሆነ ለቀህ ውጣ ሊያስብል ይችላል? ሲል ዋና ሥራ አስፈጻሚዋን ጠየቀ። ዋና ሥራ አስፈጻሚዋም አዎ! ሁከት የለም ከተባለ መሬቱ የመንግሥት ነው ማለት ነው። ስለሆነም ቦታውን ልቀቅ ማለት እንችላለን ሲሉ መለሱ።


የወረዳችሁ በፕሮሰስ ካውንስል መሬቱ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ እንደተያዘ እና በ2006 ዓ.ም ከሰነድ አልባ መሬት ጋር ተያይዞ በወጣው መመሪያ መሠረት ወረዳው ለአቤቱታ አቅራቢው ካርታ እንዲሠራለት በኮሚቴ ተወስኖለታል ።እዚህ ላይ የአካባቢ ጥበቃ ነው የተዋዋለው ከሚለው ጋር አይጋጭም ? ስለዚህ ላይ ምን ይላሉ ? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ዋና ሥራ አስፈጻሚዋን ጠየቀ።ለጥያቄው ምላሽ የሰጡት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ እኛ እያስፈጸምን ያለነው የፍርድ ቤት ውሳኔን ነው ።የወረዳውን የፕሮሰስ ካውንስል ውሳኔ አይደለም ።ፍርድ ቤት መሬቱ የአካባቢ ጥበቃ እንደሆነ ወስኗል።እኛ ደግሞ በውሳኔው መሠረት ውሳኔውን እናስፈጽማለን ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የአካባቢ ጥበቃ የእኔ ነው ሳይል እንዴት የወረዳው ሥራ አስፈጻሚ የአካባቢ ጥበቃ ነው ሊል ቻለ ሲል የአካባቢ ጥበቃ ለአቶ ስንታየሁ የጻፈውን ደብዳቤ ባሳየ ጊዜ የወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ መረጃ ከፈለክ እኔ የምልህን አዳምጥ እንጂ አትከራከረኝ ሲሉ መለሱ።እኛም መረጃው እንዳይቋረጥ በማሰብ ክርክሩን አቁመን እርሳቸውም ማዳመጡን ቀጠልን።እኛ ተፈጻሚ እያደረግን ያለነው ፍርድ ቤት ቦታውን ለቆ እንዲወጣ ያዘዘውን ውሳኔ ነው ።የፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈጻሚ መደረግ አለበት ።ይህን ተፈጻሚ ለማድረግ ደግሞ ግብር ኃይል በሕግ የተሰጠ መብት አለው ።አሁንም ደግሜ እናገራለሁ ቦታው አሁንም የአካባቢ ጥበቃ ነው ።የአካባቢ ጥበቃም በ2013 ዓ.ም ቦታው በ10 ቀናት ውስጥ ጸድቆ ወደ መንግሥት እንዲመለስ ጠይቀዋል ሲሉ ቀድመውን ሃሳባቸውን ንዴት በተሞላበት አኳኋን ደገሙልን።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በቁጥር 203/20-01/2793 በቀን 9/8/2011 ዓ.ም ለአቶ ስንታየሁ በጻፈው ደብዳቤ እንዳመለከተው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ድል በር ወደ እግዚአብሄር አብ በሚወስደው መንገድ ወንዝ ዳርቻ አጠገብ በሚገኘው የመኪና እጥበት አገልግሎት እየሠሩ ባለበት ቦታ በውል የተሰጠዎት ፈቃድ መቆረጥ እና የንግድ ምዝገባ ፍቃድ ለጊዜው በመታገዱ ምክንያት ይህ ትዕዛዝ እንዲነሳልዎት በ01/8/2011 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል።

ሆኖም መሥሪያ ቤታችን ከተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት እየሠሩበት ያለው ይዞታ የአረንጓዴ ክልል ውጪ በመሆኑ በይዞታው የማስተዳደርም ሆነ ፈቃድ የመስጠት ስልጣን እና ኃላፊነት የሌለን መሆኑን እያሳወቅን ነገር ግን በጉድጓድ ውሃ እና ለሥራው ከሌላ ቦታ ውሃ በማምጣት ተጠቅመው በድጋሚ በሪሳይክል በማጣራት የሚያከናውኑ ከሆነ ፕሮጀክቱ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (ዒአይ ዔ) በኩል ማለፍ ስላለበት ይህንን አሟልተው ሲመጡ አገልግሎት የምንሰጥዎት መሆኑን እንገልጻለን ።ግልባጭ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ፣ ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ፣ ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ንዑስ አረንጓዴ ልማት ጽሕፈት ቤት እና ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ፍትህ ጽሕፈት ቤት ይላል።ስለዚህ ምን ይላሉ? ስንል ዋና ሥራ አስፈጻሚዋን ጠየቅን ።

ወይዘሮ ደራርቱም ደብዳቤውን ለእኛ ስላልተጻፈልን



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የጉለሌ ክ/ከተማ አስተዳደር
CITY GOVERNEMENT OF ADDIS ABABA
GULLELE SUB–CITY ADMINSTRATION

5/8/2014
ቁጥር ጉ/ክ/ከ/ዋስአ/ 1124 /14 ዓ.ም
ቀን05/08/2014

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- መረጃ ስለመጠየቅ:-

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቁጥር TU/2/6151 በቀን መጋቢት 16/2014 ዓ.ም ለጉለሌ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ በተፃፈ ደብዳቤ በክ/ከተማው ወረዳ 7 ልዩ ስሙ ድልበር አካባቢ የመኪና እጥበት ስራ በመስራት ላይ የነበሩ አቶ ስንታየሁ አየለን ጉዳይ በተመለከተ ለቀረበላችሁ ቅሬታ በመመስረት ሚዛናዊ ዘገባ ለመስራት ይቻል ዘንድ ስለጉዳዩ መረጃ እንዲሰጠን ጠይቃችሁናል፡፡

ስለሆነም ስለጉዳዩ ዝርዝር መረጃ እንደሚከተለው አቅርበናል:-

በቅድሚያ አቶ ስንታየሁ አየለ በክ/ከተማችን ወረዳ 7 ልዩ ስሙ ድልበር አካበቢ በመኪና እጥበት ስራ አካበቢ ጥበቃ ውል ገብተው የአካቢቢውን ምህዳር ሳይቀይሩ ስራ እንደሚሰሩ ተገልፆ የ5 ዓመት ፍቃድ ተሰጥቷቸዋል ወደ ተግባር የገቡ ሲሆን የውል ዘመናቸው ከተጠናቀቀ በኃላ ለተጨማሪ ዓመታት በስራ ላይ የቆዩ ቢሆንም ከገቡት ውል ውጪ የአካባቢውን ምህዳር በመቀየር እና ባልተገባ መንገድ ከመንግስት በጊዜያዊነት ለስራ የተሰጣቸውን ቦታ በ2007 ዓ.ም በግል ይዞታነት በስማቸው ካርታ ለማውጣት ባደረጉት ህገ-ወጥ እንቅስቃሴ የክ/ከተማው አስተዳደር እና የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ከህገወጥ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ቢስጠንቅቃቸው ከመታረም ይልቅ ሁከት ተፈጠረብኝ በማለት አስተዳደሩ ላይ ክስ የመሰረቱ ቢሆንም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገበ ቁጥር 237477 በቀን 15/05/2011 ዓ.ም የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 230647 በቀን 6/08/2011 ዓ.ም የሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገበ ቁጥር 176497 በቀን 28/08/2014 ዓ.ም በአስተዳሩ የተፈጠረ ሁከት የለም ሲል ውሳኔ መስጠቱ ይግበኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሆነ የሰበር ሰሚው ይህን ውሳኔ በማጽናቱ እንዲሁም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በመነሳቱ የወረዳው አስተዳደር እርምጃ የወሰደ ሲሆን ለበለጠ መረጃ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 176497 በቀን 28/08/2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ---- ገፅ አያዘን የላክንላችሁ ሲሆን የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተመልክታችሁ ሚዛናዊ ዘገባ ለመስራት እንደሚረዳችሁ እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ወ/ሮ ቆንጅት ደበላ
የጉለሌ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ
Gullele Sub city Chief Executive

ግልባጭ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
• ለከንቲባ ፅ/ቤት
አዲስ አበባ

ፋክስ/Fax ስልክ/Tel. 011 8 12 51 13
E/K
1

አናውቀውም ።ግለሰብ ነው የጻፈው ! ግለሰብ የጻፈው ደግሞ ተቀባይነት የለውም ።ግለሰብ ቢጽፈውስ ሕጋዊ የሆነ ማህተም እና ቁጥር እያለው እንዴት ተቀባይነት አይኖረውም? ሲል አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ጠየቀ። ወይዘሮ ደራርቱም በንዴት ደብዳቤው ለእኛ ስላልተሰጠ እና ስለማናውቀው ተቀባይነት የለውም ሲሉ የቀደመ መልሳቸውን ደገሙ። ይህን ደብዳቤ የጻፈው አካል በሕግ ይጠየቃል ሲሉም አከሉ።

የአካባቢ ጥበቃ በቁጥ196/18-01/2519 በቀን 11/06/ 2012 ዓ.ም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ለወረዳ 7 ንግድ እና ኢንዱስትሪ ጽሕፈት ቤት በጻፈው ደብዳቤ እንዳመላከተው የአካባቢ ጥበቃ ላልተወሰነ ጊዜ የአቶ ስንታየሁ የንግድ ፈቃድ እንዳይታደስ እንደከለከለ ነገር ግን ከላይ በተገለጸው ቀን ጀምሮ እንዳይታደስ የሚለው ክልከላ እንዲነሳ መጻፉን ያትታል፡፡ስለዚህ ምን ይላሉ? ሲል አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የወረዳውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጠየቀ።

ወይዘሮ ደራርቱም ከመጀመሪያውም ንግድ ፍቃድ እንዳያድስ አልተከለከለም ሲሉ ይናገራሉ።አንባቢያን እዚህ ላይ ፍርዱን ለእናንተው ትቻለሁ።እኛ የምናውቀው ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ ብቻ ነው ።ይህን ደብዳቤ የጻፈው አካል ራሱ ይጠየቃል ሲሉ ተናገሩ።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ቤቱን ለማሸግ ስትሄዱ ለምን በሌሊት መሄድ አስፈለገ? ሲል ሥራ አስፈጻሚዋን ጠየቀ ። ዋና ስራ አስፈጻሚዋም በግብር ኃይል ስለሆነ ነው የሚል ምላሽ ሰጡ።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በግብረ ኃይልስ ቢሆን ለምን በሌሊት ሄዳችሁ ታፈርሳላችሁ? ሲል ጥያቄውን ደግሞ ጠየቀ ። ዋና ሥራ አስፈጻሚዋም በግብር ኃይል የሚፈርስ ቤት በማንኛውም ሰዓት መሄድ ይቻላል ሲሉ መለሱ።

ይህን ተከትሎ አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በፈለጋችሁት ሰዓት ሂዳችሁ ማፍረስ ይችላል የሚል መመሪያ አለ? ሲል ጠየቀ።ወይዘሮ ደራርቱም በከፍተኛ ብስጭት ግብረ ኃይሉ አስተዳደራዊ ለሆነ እርምጃ በማንኛውም ሰዓት መሄድ ይችላል በማለት ገለጹ።

እንደዚህ የሚል መመሪያ ሊያሳዩኝ ይችላሉ ? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ዋና ሥራ አስፈጻሚዋን ጠየቀ።

ወይዘሮ ደራርቱም በንዴት በማንኛውም ሰዓት እርምጃ መውሰድ አይቻልም የሚል መመሪያ ታሳየናለህ ሲሉ ጥያቄውን በጥያቄ መለሱ።

አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በ2006 ዓ.ም የወጣው አዋጅ መመሪያ እንደሚያሳየው ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለውን አንድ አካል ማግኘት እና ማነጋገር የሚፈልግ የመንግሥት አካል ማናገር የፈለገውን ሰው ማናገር የሚችለው በሥራ ሰዓት ብቻ ነው ።ለዚያውም ባጅ አድርጎ ይላል፤ ሲል መለሰ።

ይህን ተከትሎ ወይዘሮ ደራርቱ ከላይ በፈለገን ሰዓት መሄድ እንችላለን የሚለውን አቋማቸውን ትተው እኛ በሥራ ሰዓት ነው የሄድነው የሚል ምላሽ ሰጡን ።እዚህ ላይ ፍርዱን ለሕዝብ ትቸዋለሁ።

ሌላው የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ለሥራ አስፈጻሚያ ያቀረበው ጥያቄ አቶ ስንታየሁ የተባለው ግለሰብ ሕገ ወጥ እንኳን ቢሆን እና እርምጃ ይወሰድ ቢባል የሕገ ወጡን ሰው ቤት ጣራ አፍርሳችሁ አጥር በመሥራት በሠራችሁት አጥር ላይ አሸጋችሁ ሂዱ የሚል መመሪያ አለ? እናንተ ያደረጋችሁት ይሄንን ነው ።ስለዚህ ምን ይላሉ የሚል ጥያቄ ነበር ።

ወይዘሮ ደራርቱም ቦታው በሕገወጥ መልኩ ከተያዘ እና በሕገወጥ መልኩ የያዘው አካል በፍርድ ቤት እንዲለቅ ከተወሰነ ንብረቱን ጭኖ እስከመሄድ እና እስከመውረስ የሚደርስ እርምጃ ይወሰዳል።ይህን ተከትሎ አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ሕገ ወጥ ከሆነ ቤቱን አፍርሶ እቃውን ጭኖ መውሰድ እንደሚቻል ዝግጅት ክፍሉ ይገነዘባል።የዝግጅት ክፍሉ ጥያቄ ግን ሕገወጥ ከሆነ የሕገወጡን ሰው ንብረት በማፍረስ ጭኖ መውሰድ አንድ ነገር ሆኖ እያለ የሰውየውን ጣራ አፍርሳችሁ አጥር በመሥራት አሽጉ የሚል ሕግ አለ ወይ ነው ? ወይዘሮ ደራርቱም ሕገ ወጥ ከሆነ ንብረቱም ይወሰዳል።ጣሪያ ግን አላፈረስንም ሲሉ መለሱ። ወረዳው ጣሪያ አፍርሶ አጥር ማጠሩን ዝግጅት ክፍሉ በአካል ተገኝቶ አረጋግጧል።እዚህ ላይ ፍርዱን ለአንባቢያን ትተነዋል።

ሌላው አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ለሥራ አስፈጻሚዋ ያቀረበው ጥያቄ የአሸጋችሁበት ደብዳቤ ማህተም የለውም ።እንዲታሸግ የወሰነው አካል እና ሲታሸግ የነበሩ ታዛቢዎችም ስም እና ፊርማ የለበትም ስለዚህ ምን ይላሉ? የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ ወይዘሮ ደራርቱ የታሸገበት ደብዳቤ ማህተም አለው የሚል ምላሽ ሰጥዋል።

ይህን ተከትሎ በማሸጊያ ወረቀቱ ላይ እዚያም እዚህም እንዲሁ ስማቸው ያልተገለጸ ነገር ግን ፊርማቸው ብቻ የተቀመጠ ሰዎች አሉ። ይህ ወረቀቱ ላይ ያለው ፊርማ የእናንተ አይደለም? ሲል ጠየቀ።ወይዘሮ ደራርቱ እሱን እኔ ፎረንሲክ መርማሪ አይደለሁም እሱን ማረጋገጥ አልችልም ሲሉ መልሰዋል።

አዲስ ዘመን በፕሮሰስ ካውንስል የተወሰነው ውሳኔ ስህተት ነው ይላሉ? ሲል ወይዘሮ ደራርቱን ጠይቆ ነበር ።ወይዘሮ ደራርቱም ወረዳ ወይስ ክፍለ ከተማ ፕሮሰስ ካውንስል ሲሉ ጥያቄን በጥያቄ መለሱ ።የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በወረዳው የታየውን ሲል መለሰ።ይህን ተከትሎ ወይዘሮ ደራርቱ ስለመሬቱ በወረዳው የፕሮሰስ ካውንስል አልታየም ሲሉ መለሱ።አዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በቀን 16/07/2007 ዓ.ም በወረዳ ደረጃ አስራ አንድ የወረዳ አመራሮች የወሰኑትን ውሳኔ አያውቁትም ? ሲል ጠየቀ።ወይዘሮ ደራርቱም እኛ የወረዳውን እና የክፍለ ከተማ ፕሮሰስ ካውንስል የወሰነውን አልመረመርንም።እኛ የምናስፈጽመው የፍርድ ቤትን ውሳኔ ነው በማለት መለሱ።

ፍርድ ቤት ሲወስን የፕሮሰስ ካውንስል የሥራ ክንውኖችንም መሠረት ማድረጉ የማይቀር ነው ። ስለዚህ ምን ይላሉ ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የጠየቃቸው ወይዘሮ ደራርቱ ፤ ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ ስለፕሮሰስ ካውንስሉ አይመለከተንም።እኛ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ብቻ ነው ተፈጻሚ የምናደርገው ሲሉ መለሱ።

በመጨረሻም የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የሚጠይቃቸው ጥያቄች ያበሳጫቸው ወይዘሮ ደራርቱ የጋዜጠኛውን የድምጽ መቅጃ ወረወሩ።መረጃ የሰጠንህ እኛ ቀና ሰለሆንን ነው ! የሚል ንዴት የተሞላበት ቃል ተናገሩ።ነገር ግን ቅን ስለሆኑ ሳይሆን መረጃ መስጠት ስላለባቸው እንደሆነ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

ጥያቄ መጠየቃቸው ያንገበገባቸው ወይዘሮ ደራርቱ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል በጠየቃቸው በበነጋታው አጥር ሠርተው አሽገውት የነበረውን የአቤቱታ አቅራቢ ሙሉ እቃ በፌደራል ፖሊስ ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ እንዲሁም ደንብ ማስከበር ታግዘው ጭነው ሲወስዱ በቦታው በመገኘት የፎቶ ምስል ማስቀረት ችሏል።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ መረጃ እንዲሰጡን የጉለሌ ክፍለከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚን በደብዳቤ ጠይቀን በሰጡን የደብዳቤ ምላሽ ቅሬታ አቅራቢው ከገቡት ቃል ውጪ የአካባቢውን ምህዳር በመቀየርና ባልተገባ መንገድ ከመንግሥት በጊዜያዊነት ለሥራ የተሰጣቸውን ቦታ በግል ይዞታነት በሥማቸው ካርታ ለማውጣት ባደረጉት ጥረት ከሕገወጥ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ቢነገራቸውም ከመታረም ይልቅ ሁከት ተፈጠረብኝ በማለት በአስተዳደሩ ላይ ክስ ቢመሰርቱም የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237477 በቀን 15/05/2011 ዓ/ም የከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 230647 በቀን 6/08/2011 ዓ/ም የሰበር ሰሚ ፍርድቤት በሰበር ሰሚ መዝገብ 176497 በቀን 28/08/2014 ዓ/ም በአስተዳደሩ የተፈጠረ ሁከት የለም ሲል ውሳኔ በመስጠቱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድቤትም ሆነ የሰበር ሰሚው ውሳኔ ይሄንን በማጽናቱ እንዲሁም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በመነሳቱ የወረዳው አስተዳደር ርምጃ መውሰዱን የሚገልጽ ምላሽ ሰጥተዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# አገልጋይ መሪዎችንና አርአያ ተቋማትን "በዲዮጋን ፋኖስ እናፈላልግ!?"

**ታሪኩን ሳልሰሙ ወይንም ለዘነጉ፤**

ዲዮጋን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ412 ዓ.ም ገደማ የኖረ የጥንታዊቷ ግሪክ ተወዳሽና ተጠቃሽ ዐይነ ሥውር ፈላስፋ ነበር:: ይህ ፈላስፋ በሰዎች አፍቃሬ ራስነት፣ ኃላፊነት ጠልነት፣ ስግብግብነትና እንደ ጀብድ ይቆጠር የነበረው የማኅበረሰቡ የአደባባይ ንቅዘት እያበሳጨው ውስጡን ጤና ስለነሳው ከሕብረተቡ ተገልሎ ቢኖርም፤ በበርካታ ተግባራቱ ግን "የብዙኃን ኅሊና ወኪል" ተደርጎ ይወሰድ እንደ ነበር ግለታሪኩ በዝርዝር ይነግረናል::

ዐይነ ስውሩ፤ ነገር ግን ልበ ብሩሁ ዲዮጋን፣ በአንድ ወቅት በጠራራ ፀሐይ የሚበራ ፋኖስ በእጁ አንጠልጥሎ የሰው ደን በሞላበት በደማቁ ከተማቸው ውስጥ ሲዘዋወር ያስተዋሉት የአካባቢው ሰዎች "ይኸ ሰው ለየለት!" እያሉ ሲያሙት በዝምታ እያዳመጠ ጉዞውን አላቋረጠም ነበር:: ጤንነቱን ለማረጋገጥ የፈለጉ ሰዎችም ቀረብ ብለው፤ "አንድም ዐይነ ስውር፣ አንድም ሰዓቱ የቀን እኩሌታ፤ ምን ይሁን ብለህ ነው ፋኖስ አብርተህ መንገድ ለመንገድ የምትንከላወሰው?" ብለው ሲሳለቁበት ቁጣውን ዋጥ በማድረግ፤ "እናንተ ዐይናማዎቹ የብርሃን ጌቶች! በመካከላችሁ ለሰው የሚተርፍ ታማኝ ሰው ጠፍቶ እየፈለግሁ ነው!" ብሎ ትዝብታቸውን በትዝብቱ አከሸፈባቸው::

ይህ ታሪክ ትዝ ያለው ተወዳጁ ገጣሚያችን የዲዮጋን ትዝብት የእራሱ አገር ትዝብት መሆኑን አረጋግጦ የውስጡን መራራ ስሜት በብእሩ የገለጠው እንዲህ በማለት ነበር::

"በዲዮጋን ጩኸት፤ በፀሐይ ጠራራ፣
አንድ ሰው ፈልገህ፤ ፋኖስ ብታበራ፣
... አለ ማለት ዘበት...
ከጎረምሳው አፍሮ፤ ካዛውንቱ ሽበት፣
ስንት ሺህ ሰው ቆጥረህ፤ አንድ የማትልበት፣
ሁሉም ባዶ ግርማ፤ ሁሉም ባዶ ውበት::"

የፈላስፋው የዲዮጋን "የሰው ያለህ ጩኸት" እና የገጣሚው ምፀታዊ ግጥም የሚያስተላልፉልን የጋራ መልእክት "ሰው የሚሰኝ ኅሊና አደር" የሰው ፍጡር መጥፋቱን ለመጠቆም ብቻ አይደለም:: ሰው ሆኖ በተሰጠው መንግሥታዊና ሕዝባዊ አደራ በቅንነት፣ በታማኝነትና በዝቅታ ለማገልገል ፈቃደኛ "ሰው" ያለመገኘቱን ለመግለጽ ጭምር እንጂ:: ሰው በምንፈልግበት ወቅት "ሰው ሆኖ በመገለጥ" ለሰውነታችን ክብር የሚሰጥ አገልጋይ መሪ እንኳንስ በፋኖስ ነበልባል ቀርቶ በተፈጥሮ የፀሐይ ብርሃን እየኳተንን ብንፈልግ ለማግኘት በእጅጉ መቸገራችን የጊዜያችንና የአገራችን እውነታ ነው::

> **በዘርፈ ብዙው የአገራችን አመራር ውስጥ እየታየ ያለው ይህን መሰሉ የሆያ ሰለሜ ስልት ነው፡፡ የሹሙ ርእይ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የሌሎች ህልም እንዲነገርም ሆነ እንዲሰማ የማይፈለግባቸው ተቋማት በርካቶች ናቸው፡፡ "የተሻለ ርእይና አሰራር ብንከተል ያዋጣል" ብለው ሃሳብ የሚያቀርቡ ሠራተኞች ወይንም ኤክስፐርቶች "ዐይናችሁ ላፈር" እየተባሉ ሲወገዙና በዘዴ ሲሸኙ ማስተዋልም የተለመደ ሆኗል**

**ዲዮጋናዊ የመሪ ያለህ ጩኸታችን፤**

እርግጥ ነው የልባችንንና የኅሊናችንን "ጆሮ" ሙሉ ለሙሉ ደፍነን ከሚሊዮኖች ጋር እየተተረማመስንና በሰው ጫካ ውስጥ እየኖርን "የሰው ያለህ!" እያልን መጮኹ "ጩኸታችንን ለለመዱት ምን ግዴዎች" እብደትም ቅብጠትም ተደርጎ ሊታሰብ ይችል ይሆናል:: "ከሰው መሃል ሰው ጠፍቷል" በሚል ተስፋ መቁረጥ ተውጠንና በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየተደናበርን በዲዮጋን ፍልስፍና መቆዘማችንም ከበላያችን ለተኮፈሱት "ባለስልጣኖቻችን" ትርጉም ላይሰጥ ይችል ይሆናል::

ይሄን ስንል፡- በአመራር ብቃታቸው፣ በራእይ አቅማቸው፣ በህልማቸው ብሩህነት፣ በባህርያቸው ምስጉንነት "ነዎሩ!" የሚባልላቸው "ጥቂት የሰው ሰው ሹመኞች" ከገጸ-አገር ላይ ጠፍተው ጭርሱኑ "ዳዋ" ለብሰው አንቀላፍተዋል በማለትም በእዬዬ ማላዘን ፈልገንም አይደለም:: ቤተሰብን፣ አነስተኛ ቡድኖችን፣ ቤተ እምነቶችን፣ አገርንና ግዙፍ ተቋማትን መርተው የተጨበጨበላቸው፣ በምላሹም በአደባባይ ተከብረው አንቱታን ያተረፉ ኢምንት ምሳሌዎች ዛሬም በየሙያ መስኩ ብናስስ ይጠፋሉ ብሎ መደምደሙ ከእውነታ ጋር መጋጨት ይሆናል:: ዘመንና ታሪክን እያጣቀስን፣ ኅትመት ደጉንና ቴክኖሎጂውንም እያመሳከርን "ሰው በጠፋበት ዘመን ሰው ሆነው የተገኙ" አርአያ ሰብ ቅሪቶች ብናስስም ይጠፋሉ ማለት አይቻልም::

ይህ ጸሐፊ ሺህ ዘመናት ወደ ኋላ አፈግፍጎ ፈላስፋውን ዲዮጋንን ለማስታወስና የገጣሚውን ብእር ለማስረጃነት ሊያቀርብ ወደ ፈለገበት ዋና ምክንያት ዘው ብለን በድፍረት ስንዘልቅ፤ የአገልጋይ መሪነት እጦት ምን ያህል የከበደብን ሸክም እንደሆነ እንረዳለን:: የመሪነትን መንበረ ሥልጣን ተቆናጠው፣ በታጠቁት የፖለቲካ የብረት በትር እያስፈራሩ ማን ይነካናል ባይ "ጊዜ ወለዶች" መበራከታቸውን እያየን "ኡኡታችንን ብናቀልጥ" የሚቆጣን ይኖራል ብለን አንፈራም:: በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ይህን መሰሉ ሥር የሰደደ አገርና ሕዝብ ጎታች የሹመኞች ተግባር እንዲገታም ለእግዜሩና ለመንግሥታችን አቤቱታ ብናቀርብ መልስ ሰጭ ይጠፋ ካልሆነ በስተቀር አድማጭና "እውነት ነው" ባይ እናጣለን ብለን ግን በፍጹም አንጠረጥርም::

በጨበጡት ሹመት፤ "ሺህ ሞት ቢባል ይቀላል"፤ የሚመሯቸውን የበታቾችና የሚያገለግሉትን ሕዝብ ጩኸትና እዮታ ከቁብ ሳይቆጥሩ "መሪነት ተዋጥቶልናል፣ ግባችንም ሰምሮልናል" እያሉ በሕዝብ ብዙኃን መገናኛና በፓርላማው ፊት የሚዘባነኑትን በርካታ "ከረባት ለባሾች" መመልከት ብርቃችንም፤ ድንቃችንም አይደለም:: ተጽፎ የተሰጣቸውን ሪፖርት እንኳን በአግባቡ ማንበብ ተስኗቸው አንደበታቸው እየተሳሰረ፤ "የተሰጠንን ገንቢ ሃሳብ ለወደፊቱ አርመን እንመጣለን" በማለት በአንደበታቸው እየተናዘዙ በልባቸው የሚያፌዙ "ዘመን ከሎችን" ስንሰማ ውለን ስንሰማ ማደራችን የአገራችን ፖለቲካዊ ባህል ከሆነ ሰነባብቷል::

ፓርላማ ይሉት "ሥርዓት" በአገራችን ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ስልጡኖቹ አገራት ተሞክሮ "በሥራ ሰንፈው፤ በስብሰባ የጀገኑ" ውጤት እርሙዎች "ኃላፊነቴን በአግባቡ አልተወጣሁም" ብለው ሲናዘዙ እንጂ ለመቀጣጫ ሲወገዱ ወይንም ራሳቸውን ሲያስወግዱ ሰምተንም ሆነ አይተን እንደማናውቅ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እጃችንን ጭነንም ቢሆን እውነታችንን በመሃላ ማረጋገጥ አይሳነንም::

እንኳንስ "ውጤት አልቦዎች" ከወንበራቸው ተገፍትረው ሊነሱ ቀርቶ እንዲያውም "ሕዝቡ ምን እንዳያመጣ ነው!" በሚል ውሳኔ ይመስላል፤ ወደ ተሻለ ከፍታ እየተወረወሩ "በውጭ አገራት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴዎች" እየተባሉ ለየአገራቱ መንግሥታት የሹመት ደብዳቤያቸውን ሲያቀርቡ እያስተዋልን መንደድ መከሰላችን አልቀረም:: እኛ ዜጎች በንዴት በግነን ስንንጨረጨር አለቆቻችን እየሳቁ የልባቸውን ቢሰሩ አይገርመንም፤ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ መንግሥታዊ ባህላችን ነዋ!

አንድን ታላቅ አንጋፋ ተቋም አዘቅት ውስጥ ወርውሮ ያኮላሸ "የጊዜው ሰው" በሠራተኞቹ "ጾምና ጸሎት" ከቦታው በተነሳ ማግሥት አገርን በዲፕሎማሲው መስክ እንዲወክል መሾሙን ሲሰማ "ለምሳ ሊያደርጉኝ ሲያስቡ በቁርስ ተበቀልኳቸው" ብሎ የኮሎኔል መንግሥቱን ንግግር አወላግዶ ሲናገር የሰሙት የራሱ የቅርብ ብጤዎች ናቸው:: ከአንድ ታላቅ የትምህርት ተቋም ጋር ተያይዞ የተፈጸመ መሰል ታሪክም ተደጋግሞ በአደባባይ ሲወራ ስለከረመ ብዙዎች ያስታውሱታል::

ከደቡቡ የአገራችን ክፍል መንጭቶ በሁሉም አካባቢ ሕዝቦች ዘንድ ተወዳጅ የሆነውን "ሆያ ሰለሜ" የሚለው ባህላዊ ዜማና እንቅስቃሴ በዚህ ቦታ ቢታወስ ከጉዳያችን ጋር በሚገባ የሚገጥም ይመስለናል:: የሆያ ሰለሜ አቀንቃኝ ትእይንቱን የሚከውነው የመግረፊያ ጅራፍ በእጁ ይዞ በርካታ አጃቢዎችን ከኋላው በማስከተል ነው:: አጃቢዎቹ እሱ ካሰመረውና ከሚንቀሳቀስበት አቅጣጫ እንዳያፈነግጡ በዐይነ ቁራኛ መከታተል ብቻም ሳይሆን ያፈነገጡትን ሾጥ እያደረገ ወደ መስመር ያስገባቸዋል:: ማንኛውም አጃቢ የራሴ ነፃነት አለኝ ብሎ እንዳሻው በትእይንቱ አይሳተፍም:: ይህንን አደርጋለሁ የሚል ደፋር ከተገኘ የመጨረሻው ዕጣ ፈንታ ወይ ከጨዋታው መውጣት አለያም በጅራፉ መሸንቆጥ ይሆናል::

በዘርፈ ብዙው የአገራችን አመራር ውስጥ እየታየ ያለው ይህን መሰሉ የሆያ ሰለሜ ስልት ነው:: የሹሙ ርእይ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የሌሎች ህልም እንዲነገርም ሆነ እንዲሰማ የማይፈለግባቸው ተቋማት በርካቶች ናቸው:: "የተሻለ ርእይና አሰራር ብንከተል ያዋጣል" ብለው ሃሳብ የሚያቀርቡ ሠራተኞች ወይንም ኤክስፐርቶች "ዐይናችሁ ላፈር" እየተባሉ ሲወገዙና በዘዴ ሲሸኙ ማስተዋልም የተለመደ ሆኗል::

በርካታ የአገራችን ፊት ቀደም መሪዎች ሁሌም የሚፈልጉት "እሶ እሶ" እየተባሉ እንዲካደሙ እንጂ፤ የሚመሩትን ሠራተኛና የተገልጋዮችን አስተያየቶች ለማድመጥና ለመታረም በፍጹም ዝግጁ ሲሆኑ አይስተዋልም:: ቀድሞውንስ ቢሯቸውን ማን ደፍሮት!? የቢሯቸውን ሥራ እንዲያግዙ ሳይሆን ለበረኝነት የተመረጡ በሚመስሉ ጸሐፊዎቻቸው ወይንም ልዩ ረዳቶቻቸው አማካይነት ባለጉዳዮች ሲዋከቡ ማየትን ተላምደን እንደ ባህል ስለቆጠርነው ብንሰደብም ሆነ ብንንጓጠጥ የምናልፈው "ተው ቻለው ሆዴን" እያንጎራጎርን ነው:: የአንዳንድ ሹሞች የጥበቃ ጓዶች አስተያየትማ "አፈር ከመሬት የሚደባልቅ" ብጤ ስለሆነ በእነርሱ ግልምጫ ከመዋረድ "ክብርን ከጉዳይ ማስቀደሙ" በብዙ ይሻላል::

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ባለፉት ሁለት ዓመታት እግርና ጉዳይ ጥሎት ያንኳኳቸው መንግሥታዊ ቢሮዎችና የቢሮክራቶቹን ባህርይ በተመለከተ ምን መልክ እንደነበረው ጊዜው ሲደርስ ለዘመንና ለትውልድ ምስክርነት በሚበጅ መልኩ በመጽሐፍ ጥራዝ ሰንዶ ለማቅረብ እቅድ ስለያዘ ያኔ ዝርዝሩ በሚገባ ይተነተናል:: ያለ ምንም ማዳመቅና ግነት ዛሬ አሉን በምንላቸው የኢትዮጵያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና በየሥልጣን እርከኑ ደረጃ በሚገኙት መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ መብቴና ስብእናዬ ተከብሮልኝ ጉዳዬን ፈጸምኩ ብሎ የሚመሰክር አንድ ሰው ማግኘት ከተቻለ ይህ ጸሐፊ አድራሻና ባለ አድራሻውን በስም ጠቅሶ ለማመስገን ወደ ኋላ አይልም:: አርአያ ሰብ ብቻ ሳይሆን አርአያ ተቋም (Role model) ማግኘት በአገሬ ውስጥ የሰማይ ያህል እርቆናል የምንለውም ስለዚሁ ነው:: የዲዮጋንን ታሪክና የገጣሚያችንን ብእር አስታውሰን የዘከርናቸውም "እውነታችሁን ነው" ብለን ለማመስገን ጭምር ነው::

በጥንታዊው ግሪካዊ ልበ ብርሃን ፈላስፋ ታሪክ የተንደረደርንበትን ርእሰ ጉዳያችንን የምንቋጨው የዚያኔው የግሪክ አገር ሌላ አንድ ፈላስፋ ታሪክ በማስታወስ ይሆናል:: ይህ ፈላስፋ አርኪሜደስ በመባል ይታወቃል:: ብዙዎች የሚያውቁት የዘመናዊ ሂሳብ አባት መሆኑን እንጂ የፊዚክስ ሊቅ፣ ኢንጂነር፣ የከዋክብት አጥኚ እና የሌሎች የበርካታ ሳይንሳዊ ግኝቶችም ባለቤት መሆኑን ልብ አይሉም:: አርኪሜደስ በአንድ ወቅት ለአገሩ ንጉሥ ነገሥት የተሠራለት ዘውድ "ንጹሕ ወርቅ ነው አይደለም? ከሆነስ እንዴት ይረጋገጣል?" የሚል ፈታኝ ጥያቄ ቀርቦለት እንቆቅልሹን ለመፍታት ረጂም ቀናት ጠይቆት ነበር ይባላል::

አርኪሜደስን እረፍት የነሳው ይህ ፍቺ አልባ ውስብስብ ጥያቄ ቶሎ ምላሽ ሊገኝለት ባለመቻሉ ወደ ብስጭት መርቶት እንደነበርም ይነገራል:: አንድ ቀን ግን በገንዳ ውሃ ሞልቶ ሰውነቱን እየታጠበ እያለ ድንገት የእንቆቅልሹ ምሥጢር ስለተገለጠለት እንዳበደ ሰው ከገንዳው ውስጥ መለመላውን ዘሎ በመውጣት "Eureka! Eureka!"፤ "እንደተመኘሁሽ አገኘሁሽ"፤ እንዲሉ "መልሱን አገኘሁት! አገኘሁት!" እያለ እርቃኑን በከተማው ውስጥ እንደዞረ ታሪኩ በግልጽነት ይነግረናል::

እኛም በአገራችን ውስጥ እንቆቅልሽ አብዝተውብን ለእምባና ለምሬት የዳረጉን "እሽ አትበሉን የሹም ዶሮ ነን" ባይ "ባለሥልጣን" መሪዎቻችን ወደ አገልጋይ መሪነት ደረጃ ዝቅ ብለው የሚመሯቸውን ሠራተኞችና ተቋማቸውን በአርአያነት ማስመስገናቸውን ያየንና የሰማን እለት ስእለትና ምስጋና የምናቀርበው ተባብረን ነው:: እምባችን ፈስሶ ላለቀው ለእኛ ለተገልጋዮችም ዝቅ ብለው ማገልገልን ያሳዩን ዕለት ልክ እንደ አርኪሜደስ ይሉኝታ ሳይገድበን በየሚዲያው ገጾችና አየሩ ላይ እየፋነንን "Eureka! Eureka!" አገራችን አገልጋይ መሪዎችን አገኘች! ፈጣሪና መንግሥታችንም ብሶታችንንና ጸሎታችንን ሰምተው "እምባችንን አበሱልን!" እያልን መጮኻችን አይቀርም:: ሰላም ይሁን!

# የፍራንኮቫሉታ ጠቀሜታና ሲደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁን ወቅት የውጭ ምንዛሪ እጥረት እያጋጠማትና በብዙም እየተፈተነችበት እንደሆነ ይታወቃል:: ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ባለፈም ሀብቱን በአግባቡ የማስተዳደር ችግር መኖሩም ጎልቶ ይታያል:: የውጭ ምንዛሪ በእጅጉ ከሚፈለግበት ምክንያቶች መካከል በአገር ውስጥ የማይገኙ የተለያዩና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ምርቶችን ከውጭ ገበያ በመግዛት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት እንዲቻል የሚያደርግ ነው::

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ዘወትር ፈተና የሆነባት ኢትዮጵያ በተለይም በዘንድሮ ዓመት በከፍተኛ መጠን ችግሩ የበረታባት ስለመሆኑም ይነገራል:: የኑሮ ውድነቱም ሆነ የሸቀጦች ዋጋ መናር አገሪቷ ካለባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚገናኝ በመሆኑ ተባብሶ መቀጠሉ ሁነኛ ማሳያ ነው:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እጅጉን እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩትም የውጭ ምንዛሪ እጥረቱ አንዱ ምክንያት እንደሆነ ይጠቀሳል::

በዋነኝነት በአገር ውስጥ የማይገኙ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስፈልገው የውጭ መንዛሪ እጥረት ሲያጋጥም በተመሳሳይ ከውጭ ገበያ በሚገቡ ምርቶች ላይ እጥረት ይፈጠራል:: የምርት እጥረት መፈጠር ደግሞ ለዋጋ ንረት አይነተኛ ምክንያት ነውና የውጭ ምንዛሪ እጥረቱ በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት በአገሪቱ እየተባባሰ ለመጣው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት የጎላ ድርሻ አበርክቷል።

በአገሪቱ እየታየ ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለማቃለል ታዲያ መንግሥት በተለያየ ጊዜ የተለያዩ መመሪያዎችን በማውጣት ችግሩን ለማቃለል ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል:: መንግሥትከወሰዳቸውእርምጃዎች መካከል የአገር ውስጥ ምርትን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ በተወሰነ መጠን መጠቀም መቻሉ አንዱ ሲሆን፤ በዚህ መንገድ የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሪም እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ ለሆኑ ምርቶች ሲያውል ይስተዋላል:: ለአብነትም መድኃኒትን ጨምሮ የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች ማለትም የህጻናት ወተት፣ የምግብ ዘይትና ሩዝ እንዲሁም ለሌሎች መሰረታዊ የሆኑ ምርቶችን ሲያስገባ ቆይቷል::

መንግሥት በድጎማ ወደ አገር ውስጥ ከሚያስገባቸው የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች በተጨማሪ በርካታ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡት አስመጪና ላኪ የተባሉት ትላልቅ ነጋዴዎች እንደሆነ ይታወቃል:: አስመጪና ላኪው በሚያገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን ልክ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ ሲሆን፤ ነጋዴው የውጭ ምንዛሪ እጥረት በገጠመው ጊዜም የምርት እጥረት የሚፈጠር ይሆናል:: የምርት እጥረቱን ተከትሎም የዋጋ መናር ይከሰታል:: በመሆኑም ነጋዴው አገሪቱ ልትሻገር ያልቻለችው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ማቃለል ያስችላል ያለውን አማራጭ ሁሉ መጠቀም እንዲችል ሲጠይቅ ቆይቷል:: የውጪ ምንዛሪ እጥረቱን ለማቃለል ነጋዴውን ጨምሮ የተለያዩ ሰዎች ከሚያነሱት ሀሳብ መካከል ፍራንኮቫሉታ ይፈቀድ የሚለው አንዱ እንደነበር ባለሙያዎች ያነሳሉ::

እንደምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ገለጻ፤ ፍራንኮቫሉታ ማለት የውጭ ምንዛሪ ከአገር ውስጥ ሳይወጣ ነጋዴዎች በራሳቸው መንገድ ምርቶችን ከውጭ ገዝተው ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚቻልበት አሰራር ነው:: ይህም ዕቃው እጅጉን የሚፈለግ በመሆኑ አስመጪው የውጭ ምንዛሪውን ከአገር ውስጥ ሳያወጣ በራሱ የውጪ ምንዛሬ ማግኛ መንገድ ምርት ከውጪ ገዝቶ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባበትን አሰራር መፍጠር ነው::

አገር ውስጥ መግባት ያለባቸው እንደ መድኃኒት፣ የምግብ ሸቀጦችና ሌሎችንም ምርቶች ወደ አገር ውስጥ በፍራንኮቫሉታ ለማስገባት የራሱን የውጭ ምንዛሪ ይጠቀማል:: በመሆኑም አስቀድሞ በአገር ውስጥ ከውጭ ገበያ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ምርቶች አስመጪው ፈቃድ ይሰጠኝ ብሎ የሚጠይቅ ይሆናል:: ይሁንና የውጭ ምንዛሪው ያለው መሆኑ ተጣርቶ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ሂደቶችን በማለፍ ባንኮች እርስ በርስ መረጃ ተለዋውጠው ገንዘቡ የሚከፈልበትና ምርቱ ወደ አገር ውስጥ የሚገባበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ ዕቃው ተገዝቶ ወደ አገር ውስጥ ይገባል::

ይሁንና ሂደቱ እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ መካሄድ ያለበት ስለመሆኑም ባለሙያዎች አጽንኦት በመስጠት ያነሳሉ:: ይህም ሲባል የውጭ ምንዛሪው በምን መንገድ የተገኘና ከአገር ውስጥ ያልወጣ ስለመሆኑ ማረጋጋጥ በእጅጉ ጠቃሚ ነው:: ለዚህም ምክንያቱ ፍራንኮቫሉታ ይፈቀድልን የሚሉ አካላት የውጭ ምንዛሪውን ከአገር ውጭ የሚያገኙበት ሌላ መንገድ ያላቸው መሆን አለባቸው:: አሁን ባለው ሁኔታም የጥቁር ገበያው የተንሰራፋበት ሁኔታ በመኖሩና የውጭ ምንዛሪውን ከጥቁር ገበያው ገዝተው የሚያመጡ ከሆነ ህጋዊ ሂደቱን በማደናቀፍ መደፈን ያለበት ሌላ ቀዳዳ እንደመከፈት ነውና ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ሲሉ ይመክራሉ::

የፍራንኮቫሉታ መፈቀድ ኢኮኖሚውን ይበልጥ ይጎዳዋል ብለው የሚሞግቱ የምጣኔ ሀብት ምሁራን የመኖራቸውን ያክል ፍራንኮቫሉታ የበረታ ቁጥጥር ከታከለበት ለአገር ይጠቅማል ብለው ሀሳብ የሚሰነዝሩ አሉ:: ይሁንና ሁለቱንም አስታርቆ ለመጓዝና ያለውን ችግር ለመፍታት መንግሥት ወደ አገር ውስጥ ምርቶችን የሚያስገቡ አካላት ላይ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር ማድረግ አንደኛው አማራጭ ነው:: ነጋዴው ምርቱን ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ያስገባው የውጭ ምንዛሪውን ከጥቁር ገበያ ገዝቶ ነው ወይስ ከአገር ውጭ ባለው አማራጭ ተጠቅሞ ነው የሚለውን በሚገባ ማጥናት፣ መከታታልና ቁጥጥር ማድረግ የሚችልበትን መንገድ ዘርግቶ መቆጣጠር ይጠበቅበታል ሲሉም ይሞግታሉ::

ፍራንኮቫሉታ በሚፈቀድበት ጊዜ አስቀድሞ ሲታሰቡ የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። ይሄውም መጀመሪያ በንግዱ ላይ መሳተፍ ያለባቸውን ሰዎች በሚገባ ማወቅና መለየት ፤ በተለይም ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ መንግሥት በሚያስበው መንገድ ማሰብ የሚችሉ፤ አገራዊ ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት የሄደበትን ርቀት መረዳት የሚችሉና እነሱም ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጁነት ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም አስፈላጊና ተገቢ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ አለበት

ነገር ግን መንግሥት ይህን ማጣራት የሚችልበት መንገድ የሌለው ከሆነና ማጣራት ካልቻለ ሁሉም ነጋዴ ፍራንኮቫሉታ ይፈቀድልኝ በማለት ጥቁር ገበያ እንዲስፋፋ ያደርጋል:: ይህ ደግሞ ከጥቅሙ ይበልጥ ጉዳቱ አመዝኖ ከድጡ ወደ ማጡ ይሆናል ይላሉ:: የፍራንኮቫሉታ መፈቀድ ለአገር የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድነው ጉዳቱስ ምን ይሆን ስንል ላነሳነው ጥያቄ የኢኮኖሚክስ ምሁር ዶክተር ተሾመ አዱኛ ባለሙያዎች ያነሷቸውን ሀሳብ በማጠናከር የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል::

ፍራንኮቫሉታ ማለት መደበኛ የሆነ ዶላር ሳይጠይቁ ከውጭ ገበያ የተለያዩ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡበት ሥርዓት ወይም ዘዴ ነው:: ብዙ ያደጉ አገራት የዶላር ችግር የሌለባቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለያዩ ያደጉ አገራት ውስጥ ዶላር ከመንግሥት አስተዳደር ወጥቶ በገበያ ሥርዓት የሚተዳደር እንደሆነም አንስተዋል::

ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃ አገራት ከፍተኛ የሆነ የዶላር እጥረት በመኖሩና እጥረቱ ደግሞ ይበልጥ እንዳይባባስ በሚል ዶላሩን ገበያው ከሚያስተዳድረው ይልቅ መንግሥት ቢያስተዳድረው የተሻለ እንደሚሆን ታምኖበት መንግሥት እያስተዳደረው ይገኛል:: እስካሁን ያለው ሂደትም ይህንኑ ያስረዳል:: ይሁንና ይህ አሰራር በተፈለገው ጊዜና መጠን ዶላርን ማግኘት አላስቻለም:: ለዚህም ሲባል በተለያየ መንገድ ዶላር ያላቸውና ዶላሩን ማግኘት የሚችሉ ሰዎች ዶላር እንዲያመጡ መፍቀድ አንዱ አማራጭ ሆኗል::

የዶላር እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት መንግሥት ያሉትን አማራጮች ሁሉ መጠቀሙ የግድ እንደሆነ ያነሱት ዶክተር ተሾመ፤ ወደ አገር ውስጥ መግባት ያለባቸው መሰረታዊ የሆኑ ምርቶች በተለይም በአገር ውስጥ መመረት የማይችሉትን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ዶላር የግድ ይሆናል:: ዶላር የግድ አስፈላጊ እንደመሆኑም ፍራንኮቫሉታን መፍቀድ መንግሥት በአገር ውስጥ የተፈጠሩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት የሚሄድበትን ርቀት የሚያሳይ እንደመሆኑ ጥሩ ጎኑ የሚያመዝን መሆኑን ይናገራሉ:: ይህም በርካታ ጠቀሜታዎችን የሚሰጥ ነው::

መንግሥት ፍራንኮቫሉታን በፈቀደበት አግባብና መንገድ መጠቀም ከተቻለ የሚኖረው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ይገልጻሉ። አንደኛ ዶላሩን ከአገር ውጭ ጤናማ በሆነ መንገድ ማግኘት ከተቻለና የተለያዩ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ከተቻለ ምርት ይትረፈረፋል፣ የሸቀጦች ዋጋን በከፍተኛ መጠን በመቀነስ ገበያን ማረጋጋት ያስችላል:: በመንግሥት የሚታየውን የዶላር ጫናም የሚቀንስ ይሆናል:: ይህ መልካም ጎኑ ነው::

በተመሳሳይ ደግሞ ፍራንኮቫሉታ በአገር ውስጥ መፈቀዱ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖም አለው። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ሰዎች ዶላሩን ከጥቁር ገበያ ገዝተው የሚጠቀሙ ከሆነ ምንም ጥቅም አይኖረውም:: እንደውም ጉዳቱ አመዝኖ ችግሩ ይበልጥ የሚባባስበት ሁኔታ ይፈጠራል::

ምክንያቱም መንግሥት ፍራንኮቫሉታን ተጠቅመው ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ ሲፈቅድ በአገር ውስጥ ያለውን ዶላር ሳይጠቀሙ ከውጭ አገር በተለያየ አጋጣሚ በሚያገኙት ዶላር እንዲጠቀሙ ነው:: ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ዶላሩን ከጥቁር ገበያ ገዝተው ምርቶቹን ከውጭ የሚያመጡ ከሆነ አንድም መንግሥት ላይ ያለውን የዶላር ጫና መቀነስ አይችሉም:: ሁለትም የጥቁር ገበያውን ዋጋና የመደበኛውን የዶላር ዋጋ ይበልጥ ያባብሰውና የማክሮ ባላንሱ መቀነስ ሲገባው ይበልጥ እንዲጨምር ያደርገዋል::

በሶስተኛ ደረጃ ሸቀጡን በመደበኛ መንገድ በሚያስገቡበት ጊዜ ገቢና ወጪያቸው በግል የሚታወቅ በመሆኑና ነገር ግን በፍራንኮቫሉታ ወጪ ገቢያቸው የማይታወቅ በመሆኑ የመንግሥትን ገቢም ሊጎዳ የሚችልበት አጋጣሚም ይፈጠራል:: ስለዚህ ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠያቂነትን መሰረት አድርገው መሥራት ከቻሉ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል:: ካልሆነ ደግሞ ጉዳቱ የሚያመዝን ይሆናል::

መንግሥት ችግሩን ለመቅረፍ አማራጮችን ማምጣቱ መልካም ጎን ያለውና የግድ ቢሆንም ጎን ለጎን መሥራት ያለበትና መፍትሔ ነው ያለው ፍራንኮቫሉታም የበለጠ ችግር ይዞ እንዳይመጣ ምን መደረግ አለበት ስንል ላነሳነው ጥያቄም ዶክተር ተሾመ ሲመልሱ፤ ፍራንኮቫሉታ በሚፈቀድበት ጊዜ አስቀድሞ ሊታሰቡ የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። ይሄውም መጀመሪያ በንግዱ ላይ መሳተፍ ያለባቸውን ሰዎች በሚገባ ማወቅና መለየት ፤ በተለይም ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ መንግሥት በሚያስበው መንገድ ማሰብ የሚችሉ፤ አገራዊ ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት የሄደበትን ርቀት መረዳት የሚችሉና እነሱም ኃላፊነታቸውንለመወጣትዝግጁነትያላቸውሰዎችመሆን አለባቸው:: በተጨማሪም አስፈላጊና ተገቢ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ አለበት:: በተለይም ነጋዴው ዶላሩን ከየት እንደሚያመጣ ግልጽ በሆነ መንገድ አስቀድሞ ማሳየት አለበት:: ማስረጃውንም ለመንግሥት ማሳወቅ ይጠበቅበታል:: መንግሥትም እነዚህን ነገሮች ማረጋጋጥ የሚችልበትን መንገድ ዘርግቶ መከታተልና መቆጣጠር ይኖርበታል::

‹‹ብዙ ጊዜ በገባነው ቃልና ባስቀመጥነው አማራጭ የመጓዝ ከፍተኛ ችግር አለብን›› ያሉት ዶክተር ተሾመ፤ ብዙ ጊዜ በአገሪቱ በርካታ የተጀማመሩ ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲቀጥሉ የማይታዩ መሆኑንም ጠቁመዋል:: ለአብነትም ፍራንኮቫሉታ ብዙ ጊዜ ተጀምሮ ሲቋረጥ የነበረ መሆኑን አንስተው ተጀምሮ በመቋረጡ ምንድነው የተማርነው ነገር ብለን ተቋማዊ በሆነ መንገድ እና ተጠያቂነት ባለው አካሄድ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት እንዳለበትም አሳስበዋል::

ተቋማዊ በሆነ መንገድና ከፍተኛ ትኩረት በተሰጠበት አግባብ መስራት ከተቻለና ቀጣይነት እንዲኖረው ከተደረገ ፍራንኮቫሉታን በመጠቀም አገሪቷ የገጠማትን የዶላር እጥረት ማቃለልና የኑሮ ውድነቱንም ማረጋጋት ይቻላል:: ነገር ግን ፍራንኮቫሉታን መጠቀም ከሚቻልበት አግባብ ውጭ ከተጠቀምንበት ከሚሰጠው ጥቅም በበለጠ የሚኖረው ጉዳት ያመዝናልና ጥንቃቄ በተሞላበት አግባብ መከናወን ይኖርበታል በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## መጽሀፍት ሁሉ ወደ አብርሆት እንዲያመሩ እናርግ!

ዋስልኝ አየለ

ከምስራቅ አፍሪካ ግዙፍ ነው የተባለው ሁለገቡ አብርሆት ቤተ መጽሐፍ ከተመረቀ አራት ወራት ሆነው:: በእነዚህ ጊዜያት ብቻ ብዙ ተብሎለታል:: በአዲስ አበባ አራት ኪሎ ከቤተ መንግሥቱ ፊት ለፊት በዘመናዊ መልኩ የተገነባው አብርሆት፣ የማንበብ ባህልን ለማዳበር ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል እንደተባለው እየሆነ ነው::

እንደ ተመረቀ መጽሀፍ ሳላሟላ ፣ ሰራተኛ በሚገባ ሳላዘጋጅ፣ ወዘተ ሳይል ወዲያውኑ በሩን ክፍት አድርጓል፤ ይህን ተከትሎም ወጣቶች፣ ታዳጊዎች፣ ጎልማሶች፣ አዛውንቶች፣ ወዘተ ገብተው እያነበቡበት ይገኛሉ::

በ19 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው አብርሆት ማንበቢያ ብቻ ሳይሆን ማሰቢያም ሆኗል:: አዳራሹ ውስጥ ካለው ከመደበኛው ንባብ በተጨማሪ ለዓይን ማራኪ በሆነው የቤተ መጽሀፉ ክልል ውስጥ ተቀምጠው የሚመሰጡ፣ ሀሳብ የሚለዋወጡ፣ በእጃቸው የያዙትን የሚያነቡ፣ ከአካባቢው በቅርበትና በርቀት ያለውን ስፍራ ሁሉ የሚቃኙ በርካታ ናቸው::

ቤተ መጽሐፉ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት፤ ማንበቢያ ብቻ አይደለም፤ ወይም የተለመዱትን የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የአካዳሚ፣ የልቦለድ.... መጽሐፎችን ብቻ የምናነብበትም አይደለም:: ከመጽሐፍት ቤትነት በተጨማሪ አገርን የምናውቅበት ነው:: ታሪክ የሚታይበት ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ በምረቃው እለት ‹‹ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ 18 የራሳቸው አልፋቤት ካላቸው ሀገራት አንዷ፤ እንዲሁም በአፍሪካ ብቸኛዋ ብትሆንም ቤተ መጻሕፍት የላትም፤ ስለዚህም ከ18ቱ አንድ ያደረገንን የአባቶቻችን የብርሃንና የአውቀት ውጤት የሆነውን ነገር ለልጆቻችን ለማሻገር የሚያስፈልገው እንዲህ አይነት ስፍራ ነው›› ሲሉ የገለጹትም ይህንኑ ያረጋግጣል::

ከሌሎች ቤተ መጻሕፍት ለየት የሚያደርገው ሁኔታም ተመልክቼበታለሁ፤ አገርኛ ነገሮች ይበዙበታል:: በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙት ቤተ መጽሐፎች አካዳሚያዊና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ ይበዙባቸዋል:: አብርሆት ግን ገና ከጠዋቱ ብዙ በአገር ውስጥ ቋንቋዎች የተጻፉ መጽሐፎች እንዲኖሩት ተደርጓል:: እኔ እንኳ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ የተጻፉ መጽሐፎችን በዓይኔ አይቻለሁ::

አገርኛ መሆኑን የሚያሳየው ሌላው ባህሪው ደግሞ ብዙ መጽሐፎች ከሕዝብ ለማሰባሰብ መታቀዱና እየተሰበሰበ ያለበት ሁኔታ ነው:: በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ በተገኙበት በአንዲት ግለሰብ አማካኝነት በርካታ መጻሕፍት ገቢ ተደርገዋል:: ሰሞኑን ደግሞ አንጋፋው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ‹‹አምስት ሺህ መጻሕፍት በአምስት ቀን›› በሚል መርሀ ግብር ከድርጅቱ ሰራተኞች መጽሐፍ አሰባስቧል::

እንደ አንድ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሰራተኛ ከዚህ እንቅስቃሴ የተረዳሁት ቤተ መጽሐፉ የንባብ አብዮት የሚፈጠርበት መሆኑን ነው:: ምክንያቱም የሰሞኑ የሰራተኞች ወሬ ከመጽሐፍ ጋር የተያያዘም ነበርና:: ምንም እንኳን በየትኛውም ጊዜ ስለመጽሐፍ ማውራት ተገቢ ቢሆንም እንዲህ አነሳሽ ምክንያት ሲኖር ግን የበለጠ ስለመጽሐፍ ይወራል:: በሰራተኞች ከበብም ሆነ በቢሮ ውስጥ በአጋጣሚው ስለመጽሐፍና ንባብ ተወርቷል:: ይህን መጽሐፍ ብታነበው፣ ይህን መጽሐፍ ብትገዛው፣ ይህን መጽሐፍ ብታውሰኝ... የሚሉ መነቃቃቶች ነበሩ:: ይህ በራሱ ትልቅ ነገር ነው::

በሥራ እና በኑሮ ውጣውረድ ምክንያት ያሉንን መጽሐፎች እንኳን ልብ ያላልንበት ሁኔታ መስተዋሉን ያየንበትን አጋጣሚም ፈጥሮልናል:: ያነበብናቸውንና ያላነበብናቸውንም መለየት ችለናል:: አንዳንድ ሰራተኞችም መጻሕፍት የመደርደሪያ ማድመቂያ ሆነው ከሚቀመጡ በእዚህ ተቋም ተቀምጠው ያላነበቧቸው ቢያነቧቸው ብለው ለብዙ ዓመታት ያስቀመጧቸውን መጻሕፍት ለአንባቢ ይደርሱ ዘንድ ለቤተመጽሀፉ ለግሰዋል:: ደራሲያን፣ የደራሲያን ቤተሰቦችም ለግሰዋል:: ይህም የመጽሐፉን ተነባቢነት አሳዳገው ማለት ነው::

ሌላው የዚህ እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋፅኦ፤ አሁን ገበያ ላይ የሌሉ የቆዩ መጻሕፍትን ለአንባብያን እንዲደርሱ ማድረጉ ማስቻሉ ነው:: አንባብያን እነዚህን መጻፍህት በተመቻቸ ስፍራ ላይ አግኝተው እንዲያነቧቸው ማስቻሉ ትልቅ ነገር ተደርጎ ሊታይ ይገባዋል::

በእዚህ በኩል የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የመጽሀፍት ማሰባሰቡ ፊትአውራሪ በመሆን ላከናውነው ተግባር ምስጋና ሊቸረው ይገባል፤ ‹‹አምስት ሺ መጽሀፍት በአምስት ቀናት›› የሚል መርሀ ግብሩን በተሳካ ሁኔታ አጠናቆ ትናንት ለአብርሆት መጽሀፍ ቤት አስረክቧል፤ ሌሎችም ይህን አርአያነት ያለው ስራ መከተል ይኖርባቸዋል::

ድርጅቱ ከ80 ዓመታት በላይ የቆዩ የሕትመት ውጤቶች ያሉት እንደመሆኑ በርካታ አንጋፋ ሰራተኞችም ያሉበት ነው:: እነዚህ ሰራተኞች በተለያዩ ዘመናት ከገዟቸውና እንደ አይናቸው ብሌን ከሚጠብቋቸው መጻሕፍት መካከል ነው ለአብርሆት አንስተው የለገሱት:: ስለዚህ አንድ የዚህ ዘመን ወጣት አብርሆት ሲገባ አሁን ገበያ ላይ የማያገኛቸውን መጽሐፎች ያገኛል ማለት ነው::

አሁንም ሌላ ልብ ያላልናቸው ነገሮች ያሉ ይመስለኛል:: በአንዳንድ ተቋማት (ለምሳሌ በቀድሞው ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ያሉ) በመጽሐፍ ቅርጽ የሚታተሙ የተለያዩ ሰነዶችን ብዙ ጊዜ እንደ መጽሐፍ አንቆጥራቸውም:: መጽሐፍ ሲባል የግድ በታዋቂ ደራሲ የተጻፈ ብቻ አይደለም፤ በተለያዩ ባለሙያዎች አማካኝነት ተቋማት የሚያሳትሟቸው የጥናት ስብስቦችም ብዙ ዕውቀት ያሰጨብጣሉ:: እነዚህንም መጽሐፎች ለእዚህ ታላቅ ተቋም ማበርከት ይገባል::

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት መጽሀፍ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ እያደረገ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንም መጽሐፍ ማሰበሰብ ውስጥ መግባቱን ቴሌቭዥን ጣቢያው ሲያስተዋውቅ አይቻለሁ:: የእነዚህ አንጋፋ የሚዲያ ተቋማት ሰራተኞች ብዙ ታሪካዊ መጻሕፍትና ሰነዶች ስለሚኖሯቸው ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉና ይህ ጅምር በሌሎች ተቋማትም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል::

እዚህ ላይ አንድ ልብ መባል ያለበት ነገር አለ:: ንባብ ሲባል ለብዙዎቻችን ትዝ የሚለን በመጽሐፍ መልክ የታተመ ብቻ ነው:: ንባብ ማለት የትኛውም የተጻፈን ነገር ማንበብ ነው:: የቆዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች የየዘመኑን ምንነት ይገልጹልናል፤ የዚያ ዘመን ዜናዎች ለዛሬ ታሪክ ናቸው:: ስለዚህ እንደ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዓይነት አያሌ ዓመታትን ያስቆጠሩ የሕትመት ውጤቶች ያላቸው ድርጅቶች አሁን እንደ ድርጅት ለዚህ ቤተ መጽሐፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ በሚችሉበት ቁመና ላይ ናቸውና ያስቡበት እላለሁ::

በምርቃው ወቅት እንደተነገረው፤ቤተ መጽሐፉ ሰፊና ግዙፍ ነው:: ብዙ መጽሀፍትንና ሌሎች ሰነዶችን ይይዛል:: በአንድ ጊዜ ከ2 ሺህ በላይ ተጠቃሚዎችን ማስተናገድ ይችላል፤ በውስጡ ከማንበቢያ ስፍራ በተጨማሪ 8 የመጽሐፍ መሸጫ ሱቆች፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ ካፍቴሪያ፣ የህፃናትና የሚያጠቡ እናቶች ማንበቢያ ስፍራዎችንም ያካተተ ነው። በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችሉ ክፍሎችም ተዘጋጅተውለታል:: በአራት ወለሎቹ አንድ ነጥብ 4 ሚሊዮን መጻሕፍትን መያዝ የሚችል አንድ ነጥብ አምስት ኪ.ሜ መደርደሪያ አለው። በአንድ ጊዜ 115 ተሽከርካሪዎችችን ለማቆም የሚያስችል የተሟላ የመኪና ማቆሚያ አለው::

ስለዚህ አብርሆት ለየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ምቹ ነው ማለት ነው:: ከህጻናት ተማሪዎች አንስቶ እስከ ተመራማሪዎች ድረስ መገልገል ይችላሉ:: እናት ልጇን እያጠባች ፣ አካል ጉዳተኞች መውጣት መውረድ ሳይቸገሩ መገልገል የሚችሉበት ሁነታ ተመቻችቷል:: የወረቀትም (hard Copy) ሆነ የበይነ መረብ (Soft Copy) አማራጮች አሉት:: ስለዚህ ሁለገብ የሚለው ቃል ይገልጸዋል::

አብርሆት ቤተ መጽሐፍ ከተመረቀ አንስቶ ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን አጠገቡ እደርሳለሁ:: በቤተ መጽሐፉ ውስጥ ብቻ ያሉት ሳይሆኑ ከውጭ ያሉ ሰዎች የያዙትን ሲያነቡም ተመልክቻለሁ:: ራቅ ብለው ተቀምጠው በግቢው እና አካባቢው ማማር የሚመሰጡ ሳይሆኑ እንዳልቀረ የገመትኳቸውን ተመልክቻለሁ::

በአጠቃላይ አብርሆት ቤተ መጽሐፍ የማንበቢያ ብቻ ሳይሆን የማሰቢያም፣ የማስነበቢያም (መጽሐፍ በመለገስ) ሁለገብ ቤተ መጽሐፍ ነው:: እናም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ አንዳንድ ግለሰቦችና ተቋማት እንዳደረጉት ሁሉ ለእዚህ ታላቅ የማንበቢያና የማሰቢያ ተቋም መጻህፍት ሁሉ ወደ አብርሆት እንዲያመሩ በማድረግ በተቋሙ ታላቅነት ላይ አሻራችንን እናኑር!!

# ዓለም አቀፍ

## ኤለን መስክ ትዊተርን በ44 ቢሊዮን ዶላር ለመግዛት ስምምነት ላይ ደረሰ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የማህበራዊ ሚዲያው ትዊተር ቦርድ ትዊተርን በ44 ቢሊዮን ዶላር የዓለማችን ባለጸጋ ለሆነው ለኤለን መስክ ለመሸጥ ተስማማ።

ከሁለት ሳምንት በፊት ትዊተርን ለመግዛት አስደንጋጭ ሃሳብ አቅርቦ የነበረው ኤለን መስክ ትዊተር ገና ያልተፈተሸ “ትልቅ አቅም እንዳለው” ተናግሯል።

በተጨማሪም የማህበራዊ ሚዲያውን ይዘት ከማላላት በተጨማሪ ሃሰተኛ አካውንቶችን እስከ ማጥፋት ተከታታይ ለውጦች እንዲደረጉም ጠይቋል።

ኩባንያው መጀመሪያ ላይ የኤለንን ትዊተርን ልግዛ ሃሳብ ውድቅ ቢያደርግም በአሁኑ ወቅት ግን ባለ ድርሻ አካላት ስምምነቱን ለማጽደቅ ድምፅ እንዲሰጡም ሊጠይቅ ነው።

በፎርብስ መጽሄት መረጃ መሰረት 273.6 ቢሊዮን የሚገመት የተጣራ ሃብት ያለው ኤለን መስክ የአለማችን ቁጥር አንድ ባለጸጋ ነው። ይህም በዋነኝነት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አምራች በሆነው ቴስላ ባለው ድርሻ እንዲሁም ስፔስ ኤክስ የተባለውን የኤሮስፔስ ድርጅትም ይመራል።

“ነፃ ንግግር የዲሞክራሲ መሰረት ነው፤ ትዊተር ደግሞ ለሰው ልጅ የወደፊት ህይወት ወሳኝ ጉዳዮች የሚከራከሩበት የዲጂታል ከተማ አደባባይ ነው። “ሲል ኤለን መስክ ስምምነቱን ይፋ ባደረገበት መግለጫ አስታውቋል።

“በተጨማሪም ትዊተርን አዳዲስ ይዘቶች በመጨመር ማሻሻል እንዲሁም የትዊተርን አልጎሪዝም ክፍት በማድረግ መተማመንን ለመጨመር፣ አይፈለጌ ሃሰተኛ አካውንቶችን በማስወገድ እና ሁሉንም ሰው በማረጋገጥ ትዊተርን ከምንጊዜውም በላይ ማድረግ እፈልጋለሁ” ሲል አክሏል።

“ትዊተር ትልቅ አቅም አለው። ይህንንም አቅም ለማሳየት ከኩባንያው እና ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር ለመስራት እጠብቃለሁ።” በማለት አስረድቷል።

ትዊተር በይዘቱ ላይ ከፖለቲከኞችና ተቆጣጣሪዎች ላይ ከፍተኛ ጫና እየጨመረ ባለበትም ወቅት ነው ኤለን መስክ ይህንን ያሳወቀው።

የተሳሳቱ መረጃዎች በትዊተር መድረኮች ላይ መንጸባረቃቸው ከበርካታ አካላት ትችት እንዲቀርብበት ምክንያት ሆኗል።

ትዊተር ከወሰዳቸው እርምጃዎች መካከል በርካታ ተከታይ ያላቸው የቀድሞውን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕን ማገዱ ነው።

በወቅቱም ኤለን መስክ ይህንን ውሳኔም



አስመልክቶም ኩባንያው “የመናገር ነጻነት ዳኛ የመሆን ሚና በመጫወቱ በርካቶች ደስተኛ አይሆኑም” ብሏል።

## ጉቴሬዝ የምስራቅ አፍሪካ መሪዎች በዲሞክራቲክ ኮንጎና በቀጠናው ሰላም ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት አደነቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ የምስራቅ አፍሪካ መሪዎች በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎና በምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ሰላም፣ መረጋጋትና ልማትን ለማስፋፋት የሚያደርጉትን ጥረት አደነቁ፡፡

በዲ.አር ኮንጎ የሚገኙ ሁሉም የታጠቁ ቡድኖች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በፖለቲካው ሂደት እንዲሳተፉም አሳስበዋል፡፡

የዋና ጸሃፊው ተባባሪ ቃል አቀባይ ኤሪ ካኔኮ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት ከሆነ፤ ዋና ጸሃፊው የኬንያው ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታን ጨምሮ የቀጠናው መሪዎች ለዲሞክራቲክ ኮንጎ ሰላም ላሳዩት ቁርጠኝነት አመስግነዋል፡፡



ጉቴሬዝ በቀጠናው ሃይል እና በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ በተሰማራው የተባበሩት መንግስታት የሰላም ማስከበር ተልዕኮ መካከል “ውጤታማ ቅንጅት” እንደሚያስፈልግ አፅንዖት ሰጥተው መናገራቸውም ሲጂቲኤን ዘግቧል፡፡

ዋና ጸሃፊው፤ በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የሚገኙ ሁሉም የሀገር ውስጥ የታጠቁ ቡድኖች በፖለቲካው ሂደት ውስጥ “ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲሳተፉ” እና ሁሉም የውጭ ታጣቂ ቡድኖች “ትጥቅ ፈትተው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ወደየመጡበት ሀገር እንዲመለሱ” ሲሉም አሳስበዋል።

ወታደራዊ ያልሆኑ እርምጃዎችን ጨምሮ “የግጭቱን መንስኤዎች” በዘላቂነት መፍታት እንደሚያስፈልግ የተናገሩት ዋና ጸሃፊው፤ ውጥረቶችን ለማርገብ በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል ቀጣይነት ያለውና ግልጽ ውይይት እንዲደረግም ጠይቀዋል፡፡

በቀጠናው “ተጠያቂነትን ለማስፈን እንዲሁም የሰላም እና የጸጥታ ድሎችን ለማጠናከር” በሚደረጉ ጥረቶች፤ የተባበሩት መንግስታት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋልም ነው ዋና ጸሃፊው ያሉት፡፡

እንደፈረንጆቹ 2017 በሰሜን ምስራቅ ኮንጎ ዲሞክራቲክ ኮንጎ (ዲ.አር.ሲ) ጁጉ ግዛት የተቀሰቀሰው ግጭት የበርካቶችን ህይወት የቀጠፈ መሆኑና ከ230 ሺ በላይ የሀገሪቱ ዜጎች ማፈናቀሉ የሚታወቅ ነው፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ያልተዘመረላቸው የአገር ባለውለታ

አንተነህ ቸሬ

ዛሬ በዚህ አምድ የምንዘክራቸው ባለውለታችን ብዙ መልካም ተግባራትን አከናውነው ሳለ ታሪካቸውና አበርክቷቸው በሥራቸው ልክ ካልተነገረላቸው ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ የሆኑትን ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪ፣ የግብርና ሳይንስ ሊቅ፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና ፖለቲከኛ የነበሩትን ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀልን ነው፡፡

ወደ ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል ታሪክ ከመግባታችን በፊት አባታቸው ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ታሪኩን በአጭሩ እንተዋወቃቸው፡፡

ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ገና ሕፃን ሳሉ አባታቸው በሞት ስለተለዩዋቸውና አቶ ተክለወልድ የሚባሉት አጎታቸው የራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ አሽከር ስለነበሩ በራስ ዳርጌ ቤት አደጉ፡፡ በኋላም አጎታቸው ሲሞቱ የራስ ዳርጌ አገልጋይ ሆኑ፡፡ የቤተ ክህነት ትምህርት ተምረው ስለነበር የእልፍኝ ጸሐፊ ሆነው እንዲሠሩ ተሾሙ፡፡ በዚህ ሥራ ላይ ሳሉም የዋና ጸሐፊነቱን ቦታ በመያዝ ፀሐፌ ትዕዛዝ ተባሉ፡፡ በ1888 ዓ.ም ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለዓድዋ ጦርነት ሲዘምቱ ራስ ዳርጌ አዲስ አበባ ሆነው አገር እንዲያስተዳድሩ ኃላፊነት በተሰጣቸው ጊዜ ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደመስቀል የራስ ዳርጌ የቅርብ ረዳት ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከዓድዋ ድልና ከራስ ዳርጌ ሞት በኋላም በንጉሰ ነገሥቱ ልዩ ጽሕፈት ቤትና በእቴጌ ጣይቱ እልፍኝ ውስጥ ሰርተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጽሕፈት ሚኒስትር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፕሬዘዳንትና የእርሻ ሚኒስትር ሆነው እንዳገለገሉም ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ላይ በተጣለው የቦምብ አደጋ ተጠርጥረው ወደ አዚናራ ደሴት ተወስደው ታስረው ነበር፡፡ የፋሺስት ጦር ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላም በልዩ ልዩ መንግሥታዊ ኃላፊነቶች ሲያገለግሉ ቆይተው ባጋጠማቸው የጤና እክል ምክንያት በ1947 ዓ.ም አርፈዋል፡፡

ፀሐፌ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ታሪኩ እና ወይዘሮ ደስታ አየለ በትዳር ተጣምረው ከመሰረቱት ቤተሰብ በ1897 ዓ.ም የተወለደው ልጅ ማኅተመሥላሴ ተባለ፡፡ ማኅተመሥላሴ ሰባት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ያደገው ቡልጋ ውስጥ ወይን አምባ ተብሎ በሚታወቀው ሥፍራ ነው፡፡ የአማርኛ ትምህርት መማር የጀመረውም እዚያው ነው፡፡ ሰባት ዓመት ሲሞላው ደግሞ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በቤቱ ውስጥ መምህር ተቀጥሮለት የአማርኛ ትምህርቱን መማር ቀጠለ፡፡ የአማርኛ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀም ከ1907 እስከ 1913 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማረ፡፡ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ያጠናውም በዚህ ወቅት ነበር፡፡

ከ1914 እስከ 1916 ዓ.ም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀጥሮ ሠርቷል፡፡ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀጥሮ ይሠራ በነበረበት ወቅት፣ በኅዳር ወር 1915 ዓ.ም፣ ከወይዘሮ አምሳለወርቅ ክፈተው ጋር ትዳር መሰረተ፡፡ በ1916 ዓ.ም ለትምህርት ወደ ግብፅ ሄዶ አንድ አመት ከቆየ በኋላ ወደ ፈረንሳይ አቀና፡፡ በዚያም ፓሪስ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ብሔራዊ የግብርና ሳይንስ ከፍተኛ ተቋም ተምሮ በማጠናቀቅ በዲግሪ ተመርቆ በ1921 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡

እንደተመለሰም ስለትምህርቱም የዳግማዊ ምኒልክን የወርቅ ሜዳይ ተሸለመ፡፡ ከውጭ አገር የቀሰመውን የእርሻ ትምህርት በሥራ ላይ እንዲያውል በአምቦ አካባቢ የእርሻ ልማት ሥራዎችን እንዲያከናውን ስለታዘዘ፣ በአካባቢው የሚገኙ የእርሻ መሬቶች በዘመናዊ መልኩ እንዲለሙና የሕዝቡም ኑሮ መሻሻል እንዲያሳይ አድርጎ አጠናቀቀ፡፡ የአምቦ ከተማ ፕላንም በዘመናዊ አሠራር እንዲቀየስና ሕዝቡም ቦታ እየተመራ ቤት እንዲሠራ አደረገ፡፡ ለዚህ ሥራውም ባለአምበሉን ‹‹የሥላሴ ኒሻን›› ሽልማት ተሸለመ፡፡

በ1926 ዓ.ም በ‹‹ባላምባራስ›› ማዕረግ የልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ የጽሕፈት ሹም ሆኖ ተሾመ፡፡ በዚህ ኃላፊነት ላይ በማገልገል ላይ ሳለ የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን ወረረ፡፡ የካቲት



ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል

12 ቀን 1929 ዓ.ም በማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ላይ በተጣለው የቦምብ አደጋ ባላምባራስ ማኅተመሥላሴ ተጠርጣሪ ሆኖ ከአባቱ ከፀሐፌትዕዛዝ ወልደመስቀል ታሪኩ ጋር ወደ አዚናራ ደሴት ተወስደው ታስረው ነበር፡፡ ከዓመት ከስድስት ወራት እስራት በኋላ ከአዚናራ ደሴት ተፈትቶ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡

የፋሺስት ኢጣሊያ አስተዳደር የኢትዮጵያን ጥንታዊ መዛግብትን በማውደም ያደረሰው በደል ቀላል አልነበረም፡፡ የአገሪቱ ቅርሶች በከንቱ ባክነውና ወድመው መቅረታቸው ያንገበገበው ባላምባራስ ማኅተመሥላሴ፣ መዛግብቱን ሰብስቦ ማስቀመጥ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ከመዝገብ ቤት የሚያገኛቸውን የጽሑፍ ማስረጃዎች በቻለው መጠን ገልብጦ ለማስቀረት ሞክሯል፡፡

ባላምባራስ ማኅተመሥላሴ የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ከተባረረ በኋላ ኢትዮጵያን ለመገንባት በተደረገው ጥረት ከግንቦት 1933 እስከ 1938 ዓ.ም ድረስ የወሎ፣ የበጌምድርና የትግራይ ጠቅላይ ግዛቶች ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ሹም ሆነው አገልግለዋል፡፡ ‹‹የክፍለ ሀገራት አመዳደብ መስታወት›› የሚል እቅድ አዘጋጅተው ለአገር ግዛት አስተዳደር ሚኒስቴር በማቅረብ ተግባር ላይ እንዲውልም አድርገዋል፡፡

እስከ 1946 ዓ.ም በእርሻ ሚኒስቴር እንዲሁም በእርሻና ከብት እርባታ ልዩ መስሪያ ቤት እስከ ሚኒስትርነት ማዕረግ ድረስ በኃላፊነት አገልግለዋል፡፡ በእርሻ ሚኒስትርነታቸው ዘመን የአምቦ የእርሻ ምርምር፣ የሾላ የከብት በረት፣ የሆለታ የወይን ልማት፣ የእንጦጦና የደብረብርሃን የበግ እርባታ ማዕከላትንና ሌሎች የግብርና ተቋማትን አቋቁመዋል፡፡ አምቦ ውሃን አዲስ አበባ ድረስ በማስመጣት የውሃውን ጠቃሚነት ለቤተ-መንግሥቱ ያስተዋወቁት ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል እንደሆኑ በታሪካቸው መዝገብ ላይ ሰፍሯል፡፡ በዚህ ጊዜም ለልዩ ልዩ ተግባራት ወደ ውጭ አገራት ተልከው ከኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጧቸውን ተልኮዎች ፈፅመዋል፤ የአዲስ አበባ ከተማ ተጠባባቂ ከንቲባም ሆነው አገልግለዋል፡፡

ከ1948 እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ደግሞ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ተጠባባቂ ሚኒስትር፣ የገንዘብ ሚኒስትር፣ የትምህርት ሚኒስትር ደኤታ እንዲሁም የሥራና መገናኛ ሚኒስትር ሆነው ሠርተዋል፡፡ የገንዘብ ሚኒስትር ሆነው በሠሩበት ጊዜም ከጠንቃቃነታቸው የተነሳ በእቅድ ላልተያዙና አዋጭነታቸው ላልተመዘኑ ሥራዎች የመንግሥት ገንዘብ ወጪ እንዳይደረግ ጠንካራ አቋም ነበራቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ምክንያት ከንጉሰ ነገሥቱ ጋር ጭምር አለመግባባት ውስጥ ይገቡ እንደነበር በታሪክ ተጽፏል፡፡

ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ለረጅም ዓመታት በልዩ ልዩ መንግሥታዊ ኃላፊነቶች ያገለገሉበት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት እስከወደቀበት ጊዜ ድረስ ከነበሯቸው መደበኛ የሥራ ኃላፊነቶች በተጨማሪ የንጉሰ ነገሥቱን መልዕክት በመያዝ፤ ልዩ ልዩ ስምምነቶችን ለመፈራረም ወደ በርካታ አገራት ተጉዘው የተሰጧቸውን ተልኮዎች ፈፅመዋል፡፡ በመጨረሻዎቹ ዓመታት የዘውድ አማካሪ እንዲሁም የብሔራዊ መርሐ ልሳን ፕሬዘዳንት ሆነውም ሠርተዋል፡፡

ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል በተለያዩ መንግሥታዊ ኃላፊነቶች ላይ ሆነው ለረጅም ዓመታት ከማገልገላቸውና ለአገር እድገት አስተዋፅዖ ከማበርከታቸው በተጨማሪ ጎላ ብሎ የሚጠቀስላቸው አበርክቶ በሥነ-ጽሑፉ ዘርፍ ያከናወኑት ተግባር ነው፡፡ እኚህ ታላቅ የሥነ ጽሑፍ ሰው በታሪክና ባህል፣ በትምህርተ ጥበባት እና በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ከአሥራ አምስት በላይ (ያልታተሙትን ሳይጨምር) መጻሕፍትን አበርክተዋል። በተለይ ‹‹ዝክረ ነገር›› የተባለው መጽሐፋቸው በብዙ ጸሐፍትና አንባቢያን አንደበት ተደጋግመው ከሚጠቀሱት ሥራዎቻቸው መካከል ዋነኛው ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በታሪክ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና አጠቃላዩን የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚዘክር/የሚዳስስ ነው። መጽሐፉ በርካታ መረጃዎች የታጨቁበት መዝገብ በመሆኑ ታሪካዊ ማስረጃዎችን ለማመሳከር የተፃፈ ነው፡፡ ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳቸውን ዋነኛ ምክንያት ሲገልፁ፡-

‹‹… ጊዜ ያሻሻለው አዲስና ጠቃሚ የሆነ የሥልጣኔ ሥራ እንዲስፋፋ የዘመኑንም እርምጃ መከተል የሚገባ ቢሆንም ስርና መሰረቱን፣ ያለውን ያገርን ልምድና ጠባይ በጭራሽ መተውና መልቀቅ የዝክረ ነገሩን መርሳት ለሰው ልጅ የተገባ ተግባሩ ሆኖ ዐይታይም፡፡ ምን ጊዜም ቢሆን ማንኛውም ነገር ከታየና ከታወቀ በኋላ ሰዓት ሲያልፍ ‹ነበር› ከመባል አይቀርም፡፡ ነገር ግን የታሪክ ሰንሰለት በመሆኑ ማንም ሰው ያለበትን ዘመንና ያለፈውን ሁኔታ ለማስተያየት ብልጫና ጉድለቱንም ለማመዛዘን ‹ነበር›ን ማወቅ አለበት፡፡ ስለዚህም ለአገር አስተዳደር በየጊዜው የሚሠራው ሕግና ደንብ ትዕዛዝና ማንኛውም ይህን የመሰለው ሁሉ እየተጠራቀመና እየተዘጋጀ ለመጪው ትውልድ መተላለፍ ይገባዋል፡፡ እንዲህ ሳይሆን ቀርቶ ያለፈው እየተረሳ ሳይሰበሰብና ሳይከማች የጊዜውን ብቻ በመከተል ወደ ፊት ለመራመድ የተፈለገ እንደሆን ግን ማስረጃው መሰረት ያልያዘ፣ አንድነት ያጣና የተበተነ ከመሆን ይደርሳል …››

‹‹ጥበበ ገራህት›› እና ‹‹ብዕለ ገራህት›› የተሰኙት መጽሐፎቻቸው ደግሞ በእርሻ ሥራ ላይ ያተኮሩና ለሥራውም መማሪያ እንዲሆኑ አስበው ያዘጋጇቸው ሥራዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ መጻሕፍት (ያልታተሙትን ጨምሮ) መካከል፡-

**ሀ). ታሪክና ባህል**

1. ዝክረ ነገር
2. የአባቶች ቅርስ
3. እንቅልፍ ለምኔ
4. አማርኛ ቅኔ ነጠላ
5. አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው
6. ስለ ኢትዮጵያ የመሬት ሥሪት አስተዳደርና ግብር
7. ያገር ባህል (ቡልጋ)
8. ባለን እንወቅበት
9. የቀድሞው ዘመን ጨዋ ኢትዮጵያዊ ጠባይና ባህል
10. ቼ በለው
11. ጉልቁ ትውልድ ዘንጉሥ ሳህለሥላሴ
12. የኛም አሉ እንወቃቸው

**ለ). ትምህርተ ጥበባት**

1. ጥበበ ገራህት
2. ብዕለ ገራህት

**ሐ). መንፈሳዊ**

1. ዕፁብ ድንቅ
2. ስም ከመቃብር በላይ
3. ሰዋስወ ሰማይ … ይጠቀሳሉ፡፡

ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ አስተማሪ የሆኑ መጻሕፍትን ከመጻፍ ባሻገር ቅርሶችን (በተለይ የጽሑፍ) ሰብስቦ በመንከባከብ ረገድ በገንዘብ የማይተመን ትልቅ ሥራ ሠርተዋል፡፡ ለዚህ አስተዋፅዖዋቸውና አርዓያነታቸውም በ1958 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት ሥነ-ጽሑፍ ሽልማት ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል፡፡ የ‹‹ብላቴን ጌታ›› ማዕረግም ተሰጥቷቸዋል፡፡ በወቅቱ ታትሞ የነበረው የሽልማት ድርጅቱ መጽሔትም እንዲህ ሲል አትቶ ነበር፡-

‹‹… ከቡርነታቸው የሰበሰቡዋቸውን ቅኔዎች በዓይነቱና በአግባቡ በማስቀመጥ በቃል በአጭሩ የሚነገሩትን ተረቶች ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውን የቤተ-ክህነትና የቤተ-መንግሥት ስርዓት ለዛ ባለው የአማርኛ ድርሰት በማቅረብ ቋሚ ሥራ በመሥራታቸው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት ሰባት ሺህ ብር ከወርቅ ሜዳሊያና ዲፕሎማ ጋር ይሰጣቸዋል …››

ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ በሽልማት ሥነ-ስርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር እንዲህ ብለው ነበር፡፡ ‹‹… አዲሱ ትውልድ የውጭ አገር ሥልጣኔና ቋንቋ በሰፊው በሚከታተልበት ጊዜ ከጥንታዊ አባቶች የተላለፈውና የሚነገረው ሁሉ በጽሑፍ ሆኖ ካልቆየ ከአገሩ መሰረታዊ ባሕል ተለያይቶ የሚቀር መሆኑን ማሰቡ መንፈስን ከብርቱ ጭንቀት ላይ የሚጥል ነበር … በጥናት በኩልም አገራችን ግራና ቀኝ ቢሄዱ የማያደናቅፍ ሰፊ መስክ ስላለ በማንኛውም ረገድ ጥልቅ ምርመራ እያደረጉ ቅርሶቻችንና ባሕሎቻችንን ለእኛም ሆነ ለዓለም ማስተዋወቁ ጠቃሚ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቶች ‹እኛም አለን እወቁልን› የሚለውን ዓላማ በመከተል ተግተው መሥራት ይኖርባቸዋል …››

ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ የኢትዮጵያ ታሪክ በጥልቀት እንዲመረመርና እንዲጠና ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፡፡ የታሪክ መጻሕፍትን ከመጻፍ ባሻገር ራሱን የቻለ የታሪክ ጥናትና ምርምር ማዕከል እንዲቋቋም በገንዘባቸውና በእውቀታቸው ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ወጣቶች የአገራቸውን ታሪክ አውቀው ነገን የተሻለ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተደጋጋሚ ምክሮችን ለግሰዋል፡፡ በአንድ ወቅትም «እኛ ኢትዮጵያውያን አገራችን ጥንታዊት መሆኗን ሥልጣኔም በመሻት አዋቂዎችና አስተዋዮች አባቶቻችን በብዙ የደከሙ መሆናቸውን በመገንዘብ ላገራችን ወጣቶችም ሆነ ወይም ለውጭ አገር ሰዎች እውነተኛውንና ምስክርም ሊሆን የሚገባውን ሁሉ እየሰበሰብን ማዘጋጀትና ለመጭውም ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ አለብን» በማለት ተናግረው ነበር፡፡

ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል በተለያዩ መስኮች ላበረከቷቸው ዘመን አይሽሬ አስተዋጽዖዎቻቸው ብዙ ሽልማቶችን አግኝተዋል፡፡ በርካታ የታሪክ ባለሙያዎችና የሕትመት ውጤቶችም ምስጋናና ውዳሴ ቸረዋቸዋል፡፡ በአገር ውስጥ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት ሥነ-ጽሑፍ ሽልማትንና የኢትዮጵያን የክብር የኮከብ ኒሻንን ጨምሮ በርካታ ሽልማቶችን አግኝተዋል፡፡ የዩጎዝላቪያን፣ የግሪክን፣ የጀርመንንና የቼኮዝሎቫኪያን የክብር ኒሻን ሽልማቶችንም ተቀብለዋል፡፡ ከመደበኛ መንግሥታዊ ኃላፊነቶቻቸው በተጓዳኝ ከ40 በላይ ለሚሆኑ ተቋማት የቦርድ አባልና ፕሬዘዳንት በመሆን አገልግለዋል፡፡ ዘመናቸውን ያለ ምንም ዕረፍትና የጊዜ ብክነት በጥንቃቄ የተጠቀሙ ሰው ናቸው፡፡ የሠሩትን ያህል ያልተዘመረላቸው መሆናቸው ግን አይካድም፡፡

በ1967 ዓ.ም መንበረ መንግሥቱን የጨበጠው ቡድን (ደርግ) የንጉሰ ነገሥቱን መንግሥት ባለሥልጣናት በቁጥጥር ስር ሲያውል ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀልም ታሰሩ፡፡ በእስር ላይ ሳሉ ባጋጠማቸው ሕመም በ1971 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ስርዓተ ቀብራቸውም በአዲስ አበባ የካ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን ተፈፅሟል፡፡ ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል በ1915 ዓ.ም በሕግ ካገቧቸው ባለቤታቸው ወይዘሮ አምሳለወርቅ ክፈተው 11 ልጆችን አፍርተዋል፡፡

# ስፖርት



## ብሄራዊ ቡድኑ ድጋፍ ያስፈልገዋል

ብርሃን ፈይሳ

ኮትዲቯር በታሪኳ ለሁለተኛ ጊዜ አዘጋጅ የሆነችበት የአፍሪካ ዋንጫ በቀጣዩ ዓመት ይካሄዳል:: ይህን ተከትሎም የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን(ካፍ) የዚህን የ34ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታ የምድብ ድልድሉን በቅርቡ ይፋ አድርጓል:: ከወራት በኋላ ለሚካሄደው የአህጉሪቷ ትልቁ የእግር ኳስ ውድድር ከመጪው ግንቦት ወር መጨረሻ አንስቶ አገራት የማጣሪያ ጨዋታቸውን ማድረግ ይጀምራሉ::

ኢትዮጵያም በምድብ አራት ከግብጽ፣ ማላዊ እና ጊኒ ጋር መደልደሏ ይታወቃል:: የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን (ዋሊያዎቹ) ዋና አሠልጣኝ ውበቱ አባተ በዚህ ዙሪያ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ድረ-ገጽ ጋር ባደረጉት ቆይታ በቅድሚያ ድልድሉን እንዴት አገኙት የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ ኢትዮጵያ የተካተተችበት ድልድል ጠንካራ ቡድኖች ያሉበት መሆኑን አስታውቀዋል::

አሠልጣኙ ግብጽ በካሜሮኑ የአፍሪካ ዋንጫ የዋንጫ ተፋላሚ የነበረች እንዲሁም በውድድሩም ትልቅ ታሪክ አላት ሲሉ ጠቅሰው፣ ከሁለተኛዋ አገር ጊኒ ጋር የቀደመ ታሪክ ቢኖረንም በወቅታዊ አቋሟ በአፍሪካ ዋንጫው 16 ውስጥ መግባት ችላለች፤ ማላዊም በተመሳሳይ:: ስለዚህም ምድቡ ጠንካራ የሚባል ነው ሲሉ አብራርተዋል::

አሠልጣኙ እንዳሉት፤ ብሄራዊ ቡድኑን እየመሩ ከማላዊ ጋር ከዚህ ቀደም በወዳጅነት ጨዋታ የተገናኙ ሲሆን፤ በአፍሪካ ዋንጫውም የነበራቸውን አቋም ለመመልከት ችለዋል:: በአንጻሩ ከግብጽ እና ከጊኒ ብሄራዊ ቡድኖች ጋር የመገናኘት እድሉን አላገኙም:: በመሆኑም ከሌሎች ጨዋታዎች በመነሳት ያላቸው ምልከታ፤ ጊኒ በጋምቢያ ተሸንፋ ከአፍሪካ ዋንጫው ውጪ እስከምትሆን


የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ዋና አሰልጣኝ ውበቱ አባተ፤

ድረስ ጥሩ ቡድን እንደነበራት ታዝበዋል::

ብሄራዊ ቡድኑ ከግብጽ ጋር ለበርካታ ጊዜያት ተገናኝቷል ያሉት አሠልጣኝ ውበቱ፣ ከሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ወዲህ መልካም ታሪክ እንደሌለ ተናግረዋል:: በብሄራዊ ቡድን ደረጃ ከግብጽ ጋር መጫወት ትልቅ ፈተና መሆኑን ገልጸዋል፤ «ከግብጽ ጋር የሚያያዙ በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም እርሱን ወደ ጎን ትተን ኳሱ ላይ ትኩረት እናደርጋለን» ብለዋል:: በመልሱ ጨዋታ ሜዳችን ቢፈቀድና ተመልካች ስታዲየም እንዲገባ ቢደረግ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚቻልም አመላክተዋል::

ተጋጣሚ ቡድኖች ይህንን ይምሰሉ እንጂ የአሠልጣኙ ዋነኛ ትኩረት ግን የራሳቸውን ቡድን በመገንባት ላይ መሆኑን ተናግረው፣ አሠልጣኙ ቡድኑን ከያዙበት ጊዜ አንስቶ ያጋጠማቸው አንድ ችግር ተጫዋቾችን ለሰፊ ጊዜ አለማግኘት መሆኑን ይጠቅሳሉ:: የቤትኪንግ ፕሪምየር ሊግ እየተካሄደ መሆኑን ተከትሎ ውድድር አቋርጦ ዝግጅት ማድረግ አለመቻል ሌላኛው ፈተና መሆኑን አስታውቀዋል:: በዚህ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ከዝግጅት ውጪ መሆን እንደማይቻልም ገልጸው፣ በተቻለ መጠን ከተጫዋቾች ጋር የአንድ ለአንድ ግንኙነት እያደረጉ መሆናቸውንም አሠልጣኙ ይጠቁማሉ::

አሠልጣኙ በቀጣይ ደግሞ በጋራ ልምምድ ወደማድረግ ይገባሉ:: የቡድኑ አባላት ከሊግ ውድድር መምጣታቸው ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውም ነው የገለጹት:: ከተለያየ የሥልጠና እና የአጨዋወት ሁኔታ የተወጣጡትን ተጫዋቾች በረጅም ጊዜ ቆይታ ወደ ቡድን እና የህብረት ስሜት እንዲገቡ ለማስቻል እንደሚሰራ አስታውቀዋል::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ቡድናቸው ከአፍሪካ ዋንጫው መልስ ከኮሞሮስ ብሄራዊ ቡድን ጋር በቅርቡ የማጣሪያ ጨዋታ አከናውኗል:: በወቅታዊ አቋም የተሻለ ከሆነው የኮሞሮስ ቡድን ጋር ከሜዳ ውጪ በተደረገው ጨዋታም መልካም ነገሮች ታይተዋል:: በቡደኑ ስብስብ ውስጥ አዳዲስ ተጫዋቾችን በማካተትም ተስፋ ለማየት ተችሏል::

በቀጣይም በአፍሪካ ዋንጫው ተካፋይ ለመሆን የሚያስችል ጥረት እንደሚያደርጉም አሠልጣኙ ይገልጻሉ:: ያሉበት ምድብ ጠንካራ ቢሆንም በርካታ የአፍሪካ አገራት ከሜዳ እጥረትና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ክልከላ እንደተጣለባቸውም ጠቁመዋል:: ከእነዚህ መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗን ጠቅሰው፣ የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ ጥረት አድርጎ ኢትዮጵያ በሜዳዋ መጫወት ከቻለች በማጣሪያው ቆይተው የውድድሩ ተካፋይ ለመሆን አተኩረው እንደሚሠሩም አመላክተዋል::

ብሄራዊ ቡድን ሲባል ከፊት ያለው ታላቁ አካል ነው ያሉት አሰልጣኙ፣ የሚወከለው ጥቂት ቁጥር ባላቸው ባለሙያዎች ይሁን እንጂ የመላው ኢትዮጵያ ነው ብለዋል:: ብሄራዊ ቡድኑ ከመንግስት፣ ከስፖርት ባለሙያዎች እንዲሁም ከስፖርት ቤተሰቡ ሰፊ ድጋፍ እንደሚፈልግም አስታውቀው፣ በቡድኑም በኩል ከየትኛውም አካል ለሚሰጥ አስተያየት ዝግጁ መሆኑን አረጋግጠዋል:: እነዚህ አካላት በመተባበር ለአፍሪካ ዋንጫው ተሳትፎ እውን መሆን እንዲሰሩም አሠልጣኝ ውበቱ አባተ ጥሪ አቅርበዋል::


### የጠፋ የሙያና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ማሣወቅ ማስታወቂያ

አቶ አብዱልጀሊል ቃዲ ዳሎ የሙያ ምዝገባ እና የሥራ ፍቃድ ምስክር ወረቀት የጠፋባቸው መሆኑን ባመለከቱት መሠረት የአጋርፋ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ በደብዳቤ ቁጥር 2092/07/14 በቀን 26/07/2014 በተጻፈዉ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ በቀን 15/07/2001 ዓ.ም የወሰዱት የሙያ ምዝገባና የሥራ ፈቃድ ምሥክር ወረቀት ጁኒየር ሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኒሽያን (JUNIOR MEDICAL LABORATORY TECHNICIAN) በመዝገብ ቁጥር JMLT= 433/2001 HPL= 123 የነበረው የምሥክር ወረቀት የጠፋ መሆኑን አሳውቆናል፡፡

ስለዚህ የባለሙያውን የሙያ እና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት አግኝቸዋለሁ፤ በእዳ ይዤዋለሁ የሚል ተቃዋሚ ካለ እስከ 15 ቀን ድረስ ይዞ ይቅረብ፡ባይቀርብ በምትኩ ተለዋጭ የምስክር ወረቀት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ጤና ቢሮ የጤናና የጤና ነክ አገልግሎቶችና ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወሳኝ የሥራ ሂደት**

### የጠፋ የሙያና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ማሣወቅ ማስታወቂያ

አቶ ኡመር ሰዋሊህ አማን የሙያ ምዝገባ እና የሥራ ፍቃድ ምስክር ወረቀት የጠፋባቸው መሆኑን ባመለከቱት መሠረት የጎሮ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ በደብዳቤ ቁጥር 514/23/2014 በቀን 14/04/2014 በተጻፈዉ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ በቀን 27/03/2005 ዓ.ም የወሰዱት የሙያ ምዝገባና የሥራ ፈቃድ ምሥክር ወረቀት ጁኒየር ክሊኒካል ነርስ (JUNIOR CLINICAL NURSE) በመዝገብ ቁጥር JCN= 13845/2005 HPL= 314 የነበረዉ የምሥክር ወረቀት የጠፋ መሆኑን አሳውቆናል፡፡

ስለዚህ የባለሙያውን የሙያ እና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት አግኝቸዋለሁ፤ በእዳ ይዤዋለሁ የሚል ተቃዋሚ ካለ እስከ 15 ቀን ድረስ ይዞ ይቅረብ፡ባይቀርብ በምትኩ ተለዋጭ የምስክር ወረቀት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ጤና ቢሮ የጤናና የጤና ነክ አገልግሎቶችና ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወሳኝ የሥራ ሂደት**

### ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም አቶ አብደላ መሀመድ የተሽከርካሪው አይነት አይሱዙ ፤ የሰሌዳ ቁጥር 3-49498 ኦሮ፣ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34HG7P36014፣ ሞዴል NPR65N፣ የሞተር ቁጥር 4HG1-544523፣ የሊብሬ ቁጥር 0256412 የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ - ጠፍቶብኛል ሲሉ በቀን 10/08/2014 አሳውቀውናል፡፡ ስለዚህ የሰሌዳ ቁጥሩን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዣለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት (15) ቀን ውስጥ ለመስሪያ ቤታችን ሪፖርት ካላደረገ ለባለ ንብረቱ ምትክ የሰሌዳ ቁጥር የሚሰጠው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የሰበታ ከተማ ትራንስፖርት ባለስልጣን**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ጌታእንዳለ በየነ ደማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B02722 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-0402369 ሞዴል UA-SCP10-AHPNK የሞተር ቁጥር 1SZ-1023927 የሊብሬ ቁጥር 218391 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 11/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ11/8/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

### የንግድ ምልክት ባለቤት የስም ለውጥ ማስታወቂያ

Dow AgroSciences LLC. (ዶ አግሮሳየንስስ ኤልኤልሲ) አድራሻው፡ 9330 Zionsville Road IN 46268, USA የሆነ ከዚህ በታች የሰፈረው የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ብቸኛ ባለቤትና ተጠቃሚ መሆኑ ከዚህ በታች በተመለከተው ማስታወቂያ ተገልጾ ይገኛል፡፡

**በኢትዮጵያ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ዝርዝር**

| ንግድ ምልክት | የማመልከቻ ቁጥር | የማስታወቂያዎቹ ቁጥርና ቀን | |
|---|---|---|---|
| | FTM/6869 | ኢትዮጵያን ሄራልድ | አዲስ ዘመን |
| STRONGAM | | ------- | Vol LXXIX -No 277-07/10/2012 |

የንግድ ምልክቱ የሚውለው ከፍ ብለው በተዘረዘሩት ማስታወቂያዎች ላይ ለተጠቀሱት ዕቃዎች ሲሆን ንግድ ምልክቱ በማስታወቂያዎቹ ላይ ይገኛል፡፡ ባለቤቱ ስሙን ወደ Corteva Agriscience LLC. (ኮርቴቫ አግሪሳይንስ ኤልኤልሲ) የለወጠ ሲሆን ይህም በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በተመዘገበ የስም ለውጥ ሰርተፊኬት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl. LXXXI No. 229 - 19/8/2014 (27/4/2022)

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም- ሞዝቮልድ ሬድሪ ኤኤስ (Mosvold Rederi AS.) አድራሻ፡- Gåseholmen Brygge, 4552 FARSUND, Norway.
2. የማመልከቻ ቁጥር፡- FTM/6317/15
3. የጥበቃ ጊዜው፡- ከ 29/01/2022 እስከ 29/01/2029
4. የንግድ ምልክት፡- MOSVOLD
5. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 6/1/2008 ዓ.ም በ Vol LXXV No. 006 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው::
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl. LXXXI No. 229 - 19/8/2014 (27/4/2022)